# ዶርጋ በኢትዮጵያ የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) በመንጠረኛ "ሐ" ካሉ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ ተካፋይ የሆነውን ግብር ከመሰብሰብ መብት ጋር በተያያዘ፤

በበቀለ ኃይለሥላሴ*

## መግቢያ

በዚህ ጽሁፍ የጊዜ ገደብና ዶርጋ የሚሉት አገላለጾች በተለዋዋጭነት የሚያገለግሉ ሊሆን የሚያመለክቱትም ክስ በማቅረብ መብት ላይ ሕግ የደነገገው የጊዜ ወሰን ካለፈ በኋላ መብቱ ሊነፈግ የሚችል መሆኑን ነው።

በግዴታዎች ሕግ አግባብ የጊዜ ገደብ ሚና የመክሰስ መብትን ቀሪ እንዲሆን ማድረግ ነው። እንዲሁም እንደመሆኑ ተገዳጅ የሆነ ሰው ማለትም አንድ ነገር ለመፈጸም በሕግ አግባብ ግዴታ የገባ ሰው እንደተከሰሰ ወዲያውኑ ሊያነሳው የሚችል የቅድሚያ መከላከያ ነው ይህም (ፐሬስክሪፕቲቭ ቴምፖሬስ) በመባል ይታወቃል።

አሁን ባለበት መልክ የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት ግብር ከፋዮች በዚህ መከላከያ ሊጠቀሙ ያስችላቸዋልን? ይህ ጥያቄ ለዚህ ጽሁፍ መንስኤ ነው፤ የግብር ሕጎች ለመልሱ ፍንጭ እንኳ የማይሰጡ በመሆናቸውም እጅግ አከራካሪ ነው።

ጥያቄውን በአዋጅ ቁጥር 173/53 (እንዳሻሻለው) ዓመትን መሠረት በማድረግ ከሚወሰነውና ከሚሰበሰበው የገቢ ግብር አኳያ ለማየት ተሞክሯል። ይህ የሆነበት ምክንያት በጽሁፉ የቀረበውን ትንታኔ በቀላሉ ለመረዳት ያስችላል ተብሎ በመታመኑ ነው። ይህ ማለት ግን የተወሰዱት አቋሞችና የተደረሰባቸው መደምደሚያዎች ለሌሎች የግብር ዓይነቶች አግባብነት የላቸውም ማለት አይደለም። አንባቢያን በነዚህ የግብር

*በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ፋኩልቲ ሌክቸረር፥ ሕግ ፋኩልቲ

ሕጎች የተደነገጉትን ሁኔታዎች ግምት ውስጥ በማስገባት የቀረቡት አስተሳሰቦች እንዲሁም የግብር ዓይነቶች የሚመለከቱ ሆነው ያገኙአቸዋል።

የዚህ ጽሁፍ የመጀመሪያ ክፍል ስለይርጋ አጠቃላይ የሆነ ማብራሪያ የቀረበበት ነው። ፀሐፊው የመከሰስ መብት ሥራ ላይ ሊውል የሚችልበትን ጊዜ ለምን መገደብ አስፈላጊ እንደሚሆን በማብራራት የዚህን ጥንታዊ የሕግ ወግ ፋይዳ ለማሳየት ይሞክራል። በክፍሉ በስተመጨረሻ የግብር ክሶች ከይርጋ ነጻ እንዲሆኑ መፈቀድ የለበትም የሚባልባቸውን ምክንያቶች የያዙና በማስከተልም በአንዳንድ አገሮች የግብር ሥርዓቶች ውስጥ ያሉትን የይርጋ ደንቦች ባጭሩ የሚያወሱ ፖራግራፎች ይገኛሉ።

የጽሁፉ ሁለተኛ ክፍል የትንታኔውን አካል የያዘ ነው። ይህም የኢትዮጵያ የሕግ ሥርዓት አሁን ባለበት መልኩ ግብር ከፋዮች በይርጋ መከላከያ እንዲጠቀሙ ያስችላቸዋል? ለሚለው ጥያቄ ፀሐፊው ምላሽ ለመስጠት ያደረገውን ሙከራ ያሳያል። ስለግዴታዎች ጽንሰ ሃሳብ ላይ በቀረበ አጭር ማብራሪያ በመጀመር በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሕግ አንቀጽ 12 ውስጥ ያሉት የይርጋ ድንጋጌዎች በግብር ክሶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል ወይ? ወደ ሚለው ጭብጥ ትንታኔ ይሸጋገራል።

በመጨረሻም የዚህ ክፍል ጽሁፍ የተለያዩ ሁኔታዎች በመውሰድ በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/53 (እንደተሻሻለው) በሠንጠረዥ "ሐ" ከተመለከቱ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ የተጣለውን ግብር ለመሰብሰብ በሚቀርቡ ክሶች የሚነሱ የይርጋ ጭብጦች እንዴት መወሰን እንደሚኖርባቸው ለማሳየት ጥረት ተደርጓል።

ይህ መለስተኛ አስተዋጽኦ የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሕጎች ሥራ ላይ የማዋልና የማስፈጸም ኃላፊነት ለተጣለባቸው በተግባር የሚገለጥ ጥቅም እንደሚኖረው ተስፋ ይደረጋል።

## 1. ፋይዳውና ተገቢነቱ

ይርጋ ወይም የጊዜ ገደብ ከጥንት የመጣ የሕግ ወግ ነው። እጅግ ማመሩ ቢያንስ ቢያንስ ከክላሲካዊው የሮማውያን የሕግ ሥርዓት ጊዜ አንስቶ እንደሆነ ይነገራል። ለዚህም "አክሲዮኒስፐርፔቹዋ" እና "አክሲዮኒስ ቴምፖራሊስ" የተባሉት የዚያ ዘመን ተነጻጻሪ አገላለጾች ቅሪት ማስረጃዎች ናቸው[1]።

ከአምስተኛው የምህረት ምእተ ዓመት አስቀድሞ በነበሩት ዘመናት የጊዜ ገደብ የነበረው ተፈጻሚነት ከሞላ ጎደል በወንጀል ክሶች ላይ ብቻ የተወሰነ ነበር። የፍትሐብሄር ክሶችን እንዲመለከት የተደረገው ከጊዜ በኋላ ነው[2]። ያም ሆኖ ዳግማዊ ቴዎዶሳስ በ424 ዓ.ም ለዚህ ጉዳይ ንጉሠ ነገሥታዊ አዋጅ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ በሮማውያን ሕግ ውስጥ አጠቃላይ የሆነ ይርጋ አልነበረም።

በዚህ አዋጅ አጠቃላይ ባሕሪ ያለው ይርጋ ሥራ ላይ ዋለ። ጊዜውም 30 ዓመትና በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ብቻ 40 ዓመት የነበረ ሲሆን የተወሰነው ጊዜ ሲያልፍ ሥራ ላይ ሳይውሉ የቀሩ የመክሰስ መብቶች ሁሉ ይከለከሉ ነበር[3]።

በአሁኑ ዘመን ያሉ የሕግ ሥርዓቶች ሁሉ ይርጋ ተፈጻሚ የሚሆንባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች እንደሚገኙባቸው ለማስረዳት እምብዛም አያስቸግርም። የኮመን ሎው ብሂል በሰፈነባቸው ሀገሮች ይርጋን አስመልክቶ ያለው ደንበኛው የሕግ አወጣጥ ሥርዓት የጉዳዮችን ዓይነት በመለየት ተፈጻሚ የሚሆንባቸው የተለያዩ የጊዜ ገደቦችን መደንገግ ነው[4]። በመሆኑም አጠቃላይ ባሕሪ ያለው ይርጋ የሚደነግግ አንቀጽ ብርቅዬ ነው። ምናልባት ይህ የሆነበት ምክንያት በነዚህ አገሮች "ላቸዝ" ወይም ከልክ ያለፈ መዘግየት በመባል የታወቀ የሕግ ወግ በመኖሩ ሳይሆን አይቀርም[5]።

በሌላ በኩል የኮመን ሎው ተጽእኖ ጨርሶ በሌለባቸው ወይም እጅግ ትንሽ በሆነባቸው አገሮች፣ ጊዜው ካለፈ በኋላ ማናቸውንም የመክሰስ መብት የሚከለክል አጠቃላይ ባሕሪይ ያለው የይርጋ ደንጋጌ አዘውትሮ ያጋጥማል። ይህ አጠቃላይ ይርጋ የጉዳዮችን ዓይነት በመለየት ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን የተለያዩ የጊዜ ገደቦች ከሚያመለክቱት ድንጋጌዎች በተጨማሪ ነው፤ ለምሣሌ በፈረንሳይ፣ በጀርመንና በደቡብ

አፍሪካ ያለው አጠቃላይ ይርጋ የ30 ዓመት ጊዜ ነው። በኢጣሊያ፣ በስዊድን፣ በሜክሲኮና በስዊዘርላንድ ይርጋው ያለው እርዝማኔ 10 ዓመት ሲሆን በሩማኒያና በሶቪየት ሕብረት ግን 3 ዓመት ብቻ ነው[6]። የጊዜ ገደብ በግልም ሆነ በሕዝብ (መንግሥት) የሕግ መስኮች የሚገኝ ነው። እዚህ ላይ በግብር ዘርፍ ያሉትን መጥቀሱን ለኋላ ትቸት በማቆየት በኢትዮጵያ የፍትሐብሄርና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጎች የሚገኙት የጥቂት የይርጋ ድንጋጌዎች ቁጥሮች በግርጌ ማስታወሻ ተመልክተዋል[7]።

ብዙ የታወቁ የሕግ ሊቃውንት የጊዜ ገደብ አስፈላጊና ጠቃሚ ስለመሆኑ ተናግረዋል። አንድ የከመን ሉው የሕግ ሊቅ ትልብዊ አድርጎ እንደገለጸው በአንድ የተወሰነ ጉዳይ ክስ የማቅረብ መብት ዝንተዓለም ሊሠራበት የሚችል ሆኖ መኖር የለበትም። ሰዎች ክስ የሚያቀርቡባቸውን ጉዳዮች በሕሊና ግምት አግባብ በሆነ ትጋት መከታተል ይኖርባቸዋል። በመሆኑም የይርጋ ደንቦች ማለትም ክሶች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንደሚኖርባቸው የሚወስኑ ደንቦች መደንገግ አለባቸው[8]።

የመክሰስ መብት ያለው አንድ ሰው ክሱን በአፋጣኝ እንዲያቀርብ ብዙውን ጊዜ ይጠበቅበታል። ክሱ ሳይቀርብ ያለፈው ጊዜ በረዘመ መጠን የዘገየው ጉዳዩን ለመከታተል ፍላጎት ባይኖረው ወይም ቸልተኛ ቢሆን ነው የሚለው የአስተሳሰብ ዝንባሌ ይበልጥ እያመዘነ ይሄዳል። ሰረኛም ጊዜ እርምጃ ሳይወሰድ መቆየት አንድም ጉዳይ በሕግ ፊት የሚያዋጣ አለመሆኑን ዘግይቶ ለመረዳት በመቻል ወይም በፍቃደኝነት ክሱ ተትቷል የሚል ግምት ያሳድራል። በመሆኑም እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ብቻ የመክሰስ መብት ሳይሰራበት መዘግየቱን በትዕግሥት ችሎ ጊዜው ካለፈ በኋላ መዘግየቱ የመክሰስ መብቱን የማስቀረት ውጤት እንዳለው መቁጠር ከሕሊና ተቃራኒ አይሆንም። ሰፊ የሆነውን የኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሕግ የማርቀቅ ታላቅ ክንውን የፈጸሙት ፕሮፌሰር ሬኔ ዳቪድ በውል ግዴታ አግባብ ይህንን ነጥብ በሚከተለው አኳኋን ገልጸውታል።

> "ይርጋ በሕግ ሥርዓቶች ሁሉ አስፈላጊ መሆኑ የታወቀ ግዴታዎች ቀሪ የሚሆኑበት አንድ መንገድ ነው። አንድ ገንዘብ ጠያቂ ለብዙ ዓመታት መብቱን ሳይሠራበት ሲቆይ መብቱ ቀሪ ሆኖዋል ብሎ ማለት ተገቢ ይሆናል። ይህ ቀሪ የመሆን ጉዳይ ምናልባት የሌላ ምክንያት ውጤት ሊሆን ይችላል። እዳውን ባለእዳው በመክፈሉ ወይም በገንዘብ ጠያቂው ምህረት በመደረጉ ምክንያት ግዴታው ቀሪ ሆኖ ይሆናል።

> ምንም እንኳን ይህ የማይሆናቸው አጋጣሚዎች መኖራቸው እውን ቢሆንም እነዚህ በልዩነት የሚታዩ ናቸው። በነዚህም አጋጣሚዎች ቢሆን ገንዘብ ጠያቂው ሥራ ላይ ለማዋል አንዳች ተድሬያ (ትጋት) ያላሳየበትን መብት ቢያጣ ቅር ሊለኝ አይገባም።"[9]

የመክሰስ መብቶች ዝንተዓለማዊ ባሕሪ ማለትም ከሳሹ ባሻው በማናቸውም ጊዜ ሊሠራባቸው ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ቢደረግ ሥጋትና መሳቀቅ የሚያስከትሉት የማኅበራዊ ኑሮ ቀውስና ምስቅልቅል የቱን ያህል ከፍተኛ እንደሆነ ለመገመት እምብዛም አያዳግትም። በእርግጥም ክስ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት ቢወሰን አስፈላጊ ነው። ተገቢውን ሕጋዊ እርምጃ አግባብ በሆነው ጊዜ ውስጥ በመውሰድ የይርጋው መቆጠር እንዲቋረጥ ያላደረገውን ባለመብት (ገንዘብ ጠያቂ) የሚጎዳ እንኳ ሆኖ ቢገኝ በእንዲህ ያለው የጊዜ ገደብ ማለፍ ክስ የማቅረብ መብት መሞቱ መገለጽ አለበት። ክስ የሚቀርብበት ጊዜ በሕግ ቢወሰንና ሁሉም እንዲያውቀው ቢገለጽ ለሕብረተሰቡ ይበጃል። እጅግ ታዋቂ የሆኑት የሕግ ምሁርና አከራካሪያን ፐቲኒዮል ይህንን ጉዳይ በሚከተሉት ቃላት ገልፀዋል።

> "አንድ ገንዘብ ጠያቂ እጅግ ሲዘገይ ወይ ክስ የማቅረብ መብቱን ያጣዋል። ለማኅበራዊ ሠላምና ሥርዓት መስፈን ሲባል ያለፈውን መሠረዝ አስፈላጊ ይሆናል። አንድ ገንዘብ ጠያቂ ምክሬት የማድረግ ፍላጎት ባይኖረው ወይንም ምንም ጥቅም ባያገኝ ይርጋ ሥራ ላይ ሊውል መቻሉ አያጠራጥርም። በዚህ ጊዜ ተጨባጭ ኪሣራ ያስከትላል። ይሁንና ክስ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለበት የመወሰን አስፈላጊነት የይርጋ ወገን መኖር አግባብ ነው ያሰኛቸዋል። ነገሩ ፍትሐዊ ሆኖ እንዲታይ ለገንዘብ ጠያቂው እርምጃ ለመውሰድ በሚያስችለው መጠን የተራዘመ ጊዜ ሕጉ መስጠቱ በቂ ቢሆን የተበጠውም ጊዜ መቆጠሩን በሚያግዱና በሚያቋርጡ ምክንያቶች ከሞላ ጎደል ባልተወሰነ መጠን ሊራዘም መቻሉ የፍትህ መሠረት የገባ የሚጠይቀውን መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ ይገኛል። እንደእውነቱ ከሆነ ይርጋ እጅግ አልፎ አልፎ የሚያስከትላቸው አስደንጋጭ ውጤቶች ተዘውታሪ ስሆኑ አግባብና ትክክለኛ ሁኔታዎች ቀስትና ማጠናከሪያ ሆኖ ከሚገኝበት እጅግ በርካታ አጋጣሚዎች ጋር ሊነጻጸሩ አይችሉም።"[10]

ይህም ሆኖ ይርጋ ያለው በጎ ገጽታዎች ከመንግሥት የፊናንስ ጥቅም ጋር ሊሰጣጡ የማይችሉ ናቸው እየተባለ ይነገራል። በኮመን ሎው ሥርዓት ላቸው ከልክ በላይ

መዘግየት መቃወሚያ ሆኖ ነኸው ባለው ግብር የመሰብሰብ መብት ላይ አይነሳም ከሚባልበት ምክንያት አንዱ ይህ መስሎ ይታያል።[11] በሌማድ ነኸው በላቸው ላይ ተመሥርቶ ከሚቀርብ መቃወሚያ ነጻ ሆኖ መቆየቱ አሁን በኮመን ሎ ሥርዓት ያለውን የይርጋ አመለካከት ያነሳሳ ይመስላል። በዚህ ሥርዓት ክሱ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ የግድ እንዲቀርብ የሚደነግግ ግልጽ ድንጋጌ ከሌለ በቀር መንግሥት ክፍያ ከመፈጸሙ አስቀድሞ በማናቸውም ጊዜ ግብሩን ለማሰባሰብ ክስ ማቅረብ ይችላል። ይሁን እንጂ ይህ ይርጋ በግብር ጉዳዮች ላይ ያለውን ተፈጻሚነት እጅግ የሚያጣብብ መስሎ የሚታይ አቀራረብ ግብር ነክ ክሶች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለባቸው የሚወሰኑ ድንጋጌዎች በመኖራቸው የለዘበ ሆኖ ይገኛል። መንግሥት እነዚህን ድንጋጌዎች እንዲያከብር ይገደዳል።[12]

ይርጋን አስመልክቶ የፈረንሳይ ብሂል ወግ አክራሪ ሆኖ የቆየ ቢሆን እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር እስከ 1920 ዓ.ም ድረስ ለመንግሥት መከፈል ያለባቸው ዕዳዎች ከሌሎች ዕዳዎች በልዩነት የታየባቸው አጋጣሚዎች አልነበሩም። በዚያ ዓመት ግን የፈረንሳይ የሕግ አውጭ አካል በአንዳንድ ተለይተው በተመለከቱ ሁኔታዎች ይርጋ በመንግሥት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ እንዳይሆን የሚደነግግ ሕግ አወጣ[13]። ፐላኒዮል "ለመንግሥት አድሉአዊ የሆነ የጊዜ ገደብ" በሚል ርዕስ ለዚሁ ሕግ የሰጡት የተቆጠበ አስተያየት በእርምጃው አምብዛም አለመደሰታቸውን ይፈነጥቃል።

> "እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ሰኔ 25 ቀን 1920 ዓ.ም የወጣው የፈረንሳይ ሕግ 11ኛ አንቀጽ ሊሠራባቸው የቆዩትን የጊዜ ገደብ ደንቦች ያቃወሰ ነው። ይኸውም ምንም እንኳን የጊዜ ገደብ የገንዘብ ጠያቂውን መብት የሚያሳጣ ቢሆንም በአንዳንድ ሁኔታዎች ለመንግሥት እንዲከፈል የተደነገገውን የገንዘብ ልክ መክፈል ያለበትን ባለዕዳ ነጻ አያደርገውም ብሎ በመደንገጉ ነው። ይህ አቋም መሠረት ያደረገው የጊዜ ገደብ ጽንሰ ሐሳብ የተንተራሰው ዕዳው እንደተከፈለ በሚያስቆጥር የሕሊና ግምት ላይ ስለሆነ መንግሥትን በሚመለከት ክፍያው አለመፈጸሙ የተረጋገጠ በመሆኑ የተባለው የሕሊና ግምት ለመንግሥት ተከፋይ መሆን ላለባቸው ዕዳዎች ሊያገለግል አይችልም የሚለውን አስተሳሰብ ነው። ባለዕዳው የጊዜ ገደብ ተጠቃሚ የሆነበትን የገንዘብ ልክ የመንግሥት ተወካይ ለሆነው ሰው የመክፈል ግዴታ ብቻ ያለበት መሆኑ የታወቀ ነገር ነው። ይሁን እንጂ የጊዜውን ገደብ መከላከያ የሚያነሳው ባለዕዳው በመሆኑና መቆጠሩ ሊቋረጥ የሚች

> ሰውም ምንጊዜም ቢሆን ዕዳው ሲታመን በሰሆኑ ባለዕዳው የጊዜው ገደብ መቆጠር ለመንግሥት አድሎዊ እንዳይሆን ለማድረግ ይችላል የሚል ፍሬም ይኖራል። ይሆን እዚሁ አስተሳሰብ ሲወርድ ሲዋረድ ከመጣው የጊዜ ገደብ ወግ ጋር ማጣጣም ያዳግታል። የመንግሥት የፋይናንስ ጥቅም በሚያደርገው ተፅእኖ ብቻ የግል ሕግ (ሲቪል ሎው) ሲገለበጥ መቻሉን ከሚያሳዩ አስተሯሚ ምሳሌዎች መካከልም አንደኛው ሆኖ ይገኛል"።[14]

ዕዳን እንደተከፈለ የሚያስቆጥረው የሕሊና ግምት ለመንግሥት ተከፋይ መሆን ያለባቸውን ዕዳዎች አይመለከትም የሚለው ሃሣብ ምንም ያህል የሚታመንበት መስሎ ቢታይም የጊዜ ገደቡ የመንግሥትን የፊስካል ጥቅም አስመልክቶ መቆጣጠር የለበትም የሚለውን አመለካከት ግን አግባብ ነው አያሰኘውም፤ ይህ የሚባልበት ዋና ምክንያት የሕሊና ግምት የጊዜ ገደብን አስፈላጊነት የሚያስረዳ ሳይሆን የጊዜ ገደብ ደንቦችን በሕግ የተቀረጹበት ምቹ መንገድ ብቻ ስለሆነ ነው።

ከፍ ብሎ የዶርጋን አስፈላጊነት ለማሳየት አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። አሁን ደግሞ የጊዜ ገደብ የመንግሥትን የፊሲካል ጥቅም በሚመለከት መቆጣጠር የለበትም የሚለው አስተሳሰብ ለምን ተቀባይነት እንደማይኖረው ለመስረዳት ያህል ከግብር ጉዳይ አንጻር የሚከተለው ቀርቧል።

ግልጽ ከሆነው ለመጀመር፣ ራሱ የግብር አሰባሰብ ተግባር ትጋትን የሚጠይቅ ነው። ምክንያቱም የመንግሥት ባጀት ቀላል ግምት በማይሰጠው ደረጃ በዚህ ላይ የሚደገፍ ስለሆነ ነው።

በግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ላይ የጊዜ ገደብ ጫና ቢደረግበትና በዚህ የጊዜ ገደብ ማለፍም ምክንያት በመንግሥት ላይ ለሚደርሰው የገቢ ማጣት ተጠያቂ ቢሆን የግብር ክሶች ባስቸኳይ እንዲቀርቡና ይህም በተራው ለግብር አሰባሰቡ ተግባር ይበልጥ ቅልጥፍናና ንቃት ለማስገኘት እንደሚረዳ ይታመናል። በተቃራኒው የዶርጋ አለመኖር ያን ያህል ለመንግሥት ገቢ ጠቀሜታ አይኖረውም። በአጠቃላይ ሲታይ ዘግይተው የሚቀርቡ የግብር ክሶች ዋጋ ቢስ እንዳይሆኑ ያለው ስጋት መዘግየቱ በረዘመ ቁጥር ከፍ እያለ ይሄዳል።

የግብር ከፋዮችን በማቅረብ ረገድ መዘግየቱ ቀጥተኛ ካልተደረገበት ሊያስከትል የሚችላቸው ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልዩ ልዩ ጎጂ ውጤቶች ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል። የተደራረቡ ውዝፍ ግብሮችን ለማስከፈል የሚቀርብን ጥያቄ ማስፈጸም ለሕብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ የሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲዘጉ ሊያደርግ ይችላል። ያላቸውንም የሠራተኛ ኃይል ለሥራ አጥነት ሊዳረግ ይችላል። ልጆችና ሌሎች ጥገኞችም የእንዲሁ ዓይነቱ አስከፊ እርምጃ ሰለባ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያለው ግምት እጅግ ከፍተኛ ነው።

የመንግሥት የማስገበር ሥልጣን ያልተገደበ የማውደምና ቅሌት ላይ የመጣል ኃይል የተጎናፀፈው እንደሆነና ግብር ደግሞ ያንድን የሥራ እንቅስቃሴ መዘጋት የሚያስከትል በመሆኑ ብቻ እንዲከፈል የቀረበውን ክስ ውጤት እንዳይኖረው ማድረግ አግባብ እንዳልሆነ የሚያስረዳ አመለካከት መኖሩ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ከዚሁ ጋር የማስገበር ሥልጣን ለሕብረተሰቡ ብልጽግና አስፈላጊ የሆኑ፣ ጠቃሚና ጥፋት የሌላቸው የሥራ እንቅስቃሴዎች እንዲዘጉ ማድረግ የለበትም። ይህ የማስገበር ሥልጣን ራሱ እንዲኖር የሚል አመለካከት እንዳለም ማስተዋል ያሻል።[15]

በዚህ የተነሣ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤት ተግቶ ባለመሥራቱ ምክንያት የተደራረቡ ውዝፍ ግብሮችን በአንድ ጊዜ ለማስከፈል የሚቀርበውን ክስ ማስፈጸም በዜጎች ላይ የሚያስከትለውን ውድቀት አሜን ብሎ እንደመቀበል ስለሚታይ በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ የማስገበር ሥልጣኑን አግባብ ባልሆነ መንገድ እንደመጠቀም ይቆጠራል። መልካም የሆነ የመንግሥት ፖሊሲ የግብር ከፋዮች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለባቸው መወሰንን ይሻል።

ከፍ ብሎ የተገለጹት አስከፊ ውጤቶች እንደማያጋጥሙ ቢታሰብ እንኳ ግብርን በመጠየቅ ረገድ መዘግየቱ ቀጥተኛ ካልተደረገበት ግብር ከፋዮች እንዲጨነቁና እንዲሰጉ ስለሚያደርግ የሥነልቡና ደህንነታቸውን ይነካል። ይህ ሥነልቡናዊ ጫና በተራው በዕለት ተዕለት ኑሮአቸው ውስጥ ጣልቃ የሚገባና ይልቁንም አዳዲስ ሥራዎች ለመጀመር አቅዶች እንዲያመጡ የማያበረታታ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ሕግ መጽሄት ሐምሌ 16, 1986 ዓ.ም

በግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቸልተኛነት ምክንያት ብዙ ግብር ከፋዮች ለምን ላልተወሰነ ጊዜ ለአእምሮ ጭንቀት ይዳረጋሉ? የግብር ክሶችን በማቅረብ ረገድ ሊደርስ የሚችለውን አላግባብ መዘግየት በይርጋ በመቆጣጠር ለግብር ከፋዮች ከእንዲህ ዓይነቱ ጭንቀት ነጻ የሚሆኑበት መንገድ እንዲፈጠርላቸው ርትዕ ይጠይቃል።

ከፍ ብሎ የተገለጹት ተፈላጊ ያልሆኑ ውጤቶች እንዳይደርሱ ለማድረግ የግብር ዕዳ መማርን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች መጠቀም ይቻላል የሚል አስተሳሰብ ይኖር ይሆናል[16]። ይሁን እንጂ ስለ ግብር ዕዳ ምህረት የሚጸናበት የሕግ አንቀጾች አፈጻጸም እንደ ደንብ ሆኖ የሚወሰነው እንደየጉዳዩ እየታየ በፍሬ ነገሮች ላይ በሚኖረው የግል ግንዛቤ መሠረት እንደሆነ ማስተዋል ያሻል። በዚህም የተነሳ ሙሉ በሙሉና በመደጋገም አግባብ ለሆኑ ሁኔታዎች ማጠናከሪያና ዋስትና በመሆን ረገድ የምህረት ድንጋጌዎች የይርጋ ድንጋጌዎችን የሚተካከሉ አይሆኑም።

የግብር ክሶችን የይርጋ ደንቦች እንዳይመለከታቸው ማድረግ ብልህነት እንዳልሆነ ለማሳየት በመሞከር ከዚህ በላይ ብዙ ተነግሯል። አሁን ደግሞ በተግባር በሚታየው ይህን አመለካከት የተሟላ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

የብዙ ሀገሮች የግብር ሕጎች ግብር የመወሰንና እንዲከፈል የመጠየቅ መብቶችን የሚመለከቱ የይርጋ ድንጋጌዎች አሏቸው። የነዚህ ድንጋጌዎች መኖር ለመንግሥት የፊስካል ጥቅም ከማድላት ይልቅ የጊዜ ገደብ ማበጀት ለሚያስገኘው ጥቅም ማድላት የተመረጠ መሆኑን ያሳያል። ቀጥሎ የተመለከቱት ፓራግራፎች ባጭሩ ጥቂቶቹን ያብራራሉ።

የብራዚል የግብር ሥርዓት የገቢ ግብር አወሳሰንንና አሰባሰብን የሚመለከት የይርጋ ውሣኔ የሚደረገው ግብር ከፋዩ ያቀረበውን የገቢ መግለጫ መሠረት በማድረግ ወይም የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በራሱ የሥራ ኃላፊነት በሚወስደው እርምጃ ነው። ይህ መከናወን ያለበት ግብሩ ከሚከፈልበት ዓመት መጨረሻ አንስቶ ባሉት የ5 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ነው።

የብራዚል ሕግ ተጨማሪ ወይም ማሟያ የግብር ውሣኔ ሊደረግ እንደሚችልም ይገልጻል። ይህ ተጨማሪ ወይም ማሟያ የሆነው የግብር ውሣኔ መደረግ ያለበት ግን ለግብር ከፋዩ የመጀመሪያው የግብር ውሣኔ ከደረሰበት ቀን እንስቶ ባለው የ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው። ይህ ማለት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የመጀመሪያውን የግብር ውሳኔ በተደነገገለት ጊዜ ውስጥ ባልሰጠበት ሁኔታ ተጨማሪ ወይም ማሟያ የሆነውን የግብር ውሣኔ ማድረግ አይችልም ማለት ነው።[17]

> "አሁን ሕጉ ባለበት ሁኔታ ከላይ የተጠቀሱት የ5 ዓመት የጊዜ ገደቦች ግብር የመወሰን መብትን ቀሪ የማድረግ ውጤት ያላቸው ወሳኝ የጊዜ ገደቦች ናቸው። መንግሥት በሚፈጽማቸው ተግባሮች መቆጠራቸው የሚቋረጥ ወይም ለጊዜው የሚታገድ አይደለም"።[18]

መንግሥት ግብር ለመሰብሰብ ያለው መብት እንዲሁ በ5 ዓመት ይርጋ ቀሪ እንዲሆን ተወስኖአል። ይርጋው መቆጠር የሚጀመረውም በግብር ውሣኔ ማስታወቂያው ላይ ግብር እንዲከፈል ከተገለጸበት የመጨረሻ ቀን እንስቶ ነው። የዚህ ይርጋ መቆጠር ሊቋረጥ ይችላል። ለምሣሌ፣ ለግብር ከፋዩ ግብሩን እንዲከፍል በሚቀርበው ጥያቄ ወይም ለግብር አከፋፈሉ በሚሰጥ ተጨማሪ የመክፈያ ጊዜ ፈቃድ፣ ግብሩ እንዲከፈል የቀረበ ክስም ካለ ክሱ እስከቀጠለ ድረስ የይርጋውም መቆጠር ለጊዜው የሚያግድ ይሆናል።[19]

በኢጣሊያ የግብር ሕጎች ውስጥ መንግሥት ያለውን ግብር የመጠየቅ መብት የሚመለከቱ በርካታ የይርጋ ድንጋጌዎች ይገኛሉ። ሥራ ላይ ያለው የሕግ አወጣጥ ዘይቤ ሁኔታዎችን ለይቶ በማመልከት በነዚሁ ላይ ተፈጻሚ የሚሆኑትን የተለያዩ የጊዜ ገደቦች መደንገግ ነው። ይህ እንግዲህ ድንጋጌዎቹ ለምን ሊበረከቱ እንደቻሉ ያስረዳል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ልዩ ሁኔታዎች ሳይነኩ የግብር አስተዳደር መ/ቤቱ አንድ ግብር ከፋይ የገቢውንና የወጪውን መግለጫ ካቀረበበት ቀን እንስቶ 3 ዓመት ካለፈ በኋላ ግብር እንዲከፈል ከመጠየቅ የተከለከለ ነው። የገቢና የወጪ መግለጫ ባልቀረበበት ሁኔታ ግን የይርጋ ጊዜ 20 ዓመት ይደርሳል። መቆጠር የሚጀምረውም መግለጫው መቅረብ ከነበረበት ቀን እንስቶ ነው።

ለግብር ከፋዩ የሚገኝ ትዕዛዝ እንዲደርሰው ማድረግ ወይም በግብር ከፋዩ ላይ አስገዳጅነት ያለው ሥነሥርዓት (ክስ) መመሥረት የይርጋውን መቆጠር ያቋርጣል። የይርጋው መቆጠር በአግባቡ ከተቋረጠ አዲስ ይርጋ እንደገና መቆጠር ይጀምራል። የዚህም የይርጋ ጊዜ ለቀድሞ (ለተቋረጠው) ይርጋ በሕግ ከተደነገገው ጋር እኩል ነው።[20]

የስዊድን የግብር ሥርዓት መንግሥት ያለው ግብር የመሰብሰብ መብት በይርጋ ቀሪ ሊሆን ስለመቻሉ የሚጠቀስ ሌላ አስደናቂ ምሳሌ ነው። በስዊድን ያለው አጠቃላይ የሆነው ደንብ የግብር መሰብሰቢያ ከሆነው ዓመት መጨረሻ አንስቶ የ5 ዓመት ጊዜ ካለፈ በኋላ በግብር ከፋይ ላይ ምንም ዓይነት የክፍያ ጥያቄ ሊቀርብ አይችልም የሚል ነው። ግብሩ ሳይከፈል የቀረው በግብር ከፋይ የወንጀል አድራጎት ቢሆን እንኳ ደንቡ ተፈጻሚ ይሆናል። ከዚህ አንጻር በስዊድን ያለው አፈጻጸም ከብዙ አገሮች የግብር ሥርዓት ሥር ነቀል (መሠረታዊ) በሆነ መንገድ ልዩነት ያሳያል።

አግባብ ያለው የግብር ባለሥልጣን መ/ቤት የተወሰነው ግብር ገቢ እንዲሆን በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ በማናቸውም ግዴታውን በማይፈጽም ግብር ከፋይ ላይ በስዊድን የፍትሐብሔር ፍ/ቤቶች ክስ ማቅረብ ይችላል። ንብረቱንም ለማስከበር ወይም የከሣራ ሥነ ሥርዓት እንዲካሄድበት ለማድረግ ማመልከት ይችላል። የዚህ ዓይነቱ እርምጃ መወሰድ መጀመሩ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የ5 ዓመቱ ይርጋ ካለፈ በኋላ እንኳ ግብሩን ለመሰብሰብ መብት እንዲኖረው ያደርጋል።[21]

የጀርመን ፌደራል ሪፐብሊክ የፊስካል ኮድ የግብር ክሶች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መቅረብ እንዳለባቸው የሚደነግጉ ዝርዝር ደንቦችን የያዘ ነው። እነዚህ ደንቦች የአወሳሰን ይርጋና የአሰባሰብ ይርጋ በማለት ልዩነት አያደርጉም። ለሁለቱም የተደነገገው ይርጋ በአጠቃላይ ሲታይ አምስት ዓመት ነው። መቆጠር የሚጀምረው ግብሩ በሚመለከተው ዓመት መጨረሻ ማለትም የግብር ከፋዩን የግብር ኃላፊነት ለመወሰን የሚያስችሉት ተጨባጭ ሁኔታዎች ሁሉ ከተደረሰባቸው ጊዜ አንስቶ ነው።[22] ግብር ከፋዩ ግብር በመሸወድ (በማጭበርበር) ወንጀል ጥፋተኛ መሆኑ በተረጋገጠበት ሁኔታ ይርጋው የሚቆይበት ጊዜ 10 ዓመት ይሆናል።

እንዚህ ደንቦች የይርጋው መቆጠር በተለያዩ ምክንያቶችና ሁኔታዎች ሊቋረጥ ወይም ሊታገድ ስለመቻሉ ይደነግጋሉ። መቆጠሩ ታግዶ ይርጋው የሚራዘምበት ሁኔታ በይርጋው መጨረሻ ባሉት ስድስት ወራት ውስጥ የሕዝብ ጠላት ወይም የተፈጥሮ መቅሰፍት ባደረሰው ችግር የተነሳ መንግሥት ግብር እንዲከፈለው ያለውን ተያቂ ለማቅረብ (ለመክሰስ) ያልቻለበት አጋጣሚ ነው።

አግባብ ያለው ያካባቢ የፊናንስ ኃላፊ የግብር ከፋዩን ማንነት ወይም ያለበትን የግብር ግዴታ ለማወቅ የሚወስደው ማናቸውም ግልጽ የሆነ እርምጃ የይርጋውን መቆጠር ያቋርጠዋል። የተሰመደ አሠራር የሆነው የገቢና የወጪ መግለጫ እንዲቀርብ መጠየቅ እንኳ የዚህ ምክንያት ሊሆን ይችላል። ግብር ከፋዩ ግዴታ ያለበት መሆኑን ማመኑ፣ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ለክፍያ የተወሰነውን ጊዜ ለማራዘም መፍቀድ የመሳሰሉ ተግባሮች ይርጋው ከሚቋረጥባቸው ምክንያቶች የሚመደቡ ናቸው። ይህ ዓይነቱ መቋረጥ ካጋጠመበት ዓመት መጨረሻ አንስቶ አዲስ ይርጋ መቆጠር ይጀምራል።

በምዕራብ ጀርመን የይርጋ ደንቦች የሚታየው አስገራሚ ገጽታ ራሱ ግብር ከፋዩ ይህንን መከላከያ እንዲያነሳው የማይጠይቁ መሆናቸው ነው። በዚህ ፈንታ ለማናቸውም የግብር ክስ ምሥረታ የጊዜ ገደቡ አለማለፍ ሥነ ሥርዓታዊ ቅድመ ሁኔታ እንዲሆን ይደነግጋሉ። በመሆኑም የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በራሱ አነሳሽነት በሥራው አካሄድ ሁሉ ለዚህ ነጥብ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። በዚህ ረገድ የምዕራብ ጀርመን ደንቦች በሌሎች የፍትሐብሔር መስኮች ካሉ የጊዜ ገደብ ደንቦች ሥር ነቀል በሆነ መንገድ (ፍጹም) ይለያሉ።

ይርጋው ከማለፉ ጋር መንግሥት ያለው የግብር ክስ የማቅረብ መብት ቀሪ ይሆናል። ከዚሁ ጋር የተገናኙትንም ወጪዎች፣ መቀጫዎችና በግብሩ ላይ ተደማሪ የሚሆኑ ሌሎች ክፍያዎች ሁሉ የማስከፈል መብቱ እንዲሁ ቀሪ ይሆናል። በመሆኑም የጊዜው ገደብ ካለፈ በኋላ ግብር ቢወሰን ውሣኔው እንዳች ውጤት አይኖረውም።[23]

በመጨረሻ የኢትዮጵያ የግብር ሥርዓት ውስጥ የመንግሥት የፊናንስ ጥቅም ባለበት ሁኔታ ይርጋ እንዲቆጠር ተደርጎ እንደሆነ ለማወቅ ጥናቱን ወደዚህ ጉዳይ

መመለስ አግባብ ሆኖ ይገኛል። በርግጥ በብዙ ረገድ ይልቁንም የይርጋ ደንቦችን በሚመለከት ትልቅ ጉድለት የሚታይባቸው በመሆኑ እንዲያ በኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሕጎች በጠቅላላ የግብር አዋጆች ውስጥ የይርጋ ድንጋጌዎች የሚያጋጥሙት እጅግ አልፎ አልፎ ነው? ይሁንና የመንግሥት የፊናንስ ጥቅም ባለበት ሁኔታ የጊዜ ገደብ የሚቆጠር መሆኑን የሚያሳዩ ሁለት ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል።

የመጀመሪያው ከጉምሩክ ቀረጥ አሰባሰብ ጋር የተዛመደ ነው። በስህተት ዕቃዎች ሊከፈልባቸው ከሚገባው ልክ ያነሰ ቀረጥ የተከፈለባቸው ሲሆን ወይም ለግብር ከፋዩ በስህተት ተመላሽ ገንዘብ እንዲወስድ የተደረገ ሲሆን ልዩነቱ እንዲከፈል ወይም አለአግባብ ተመላሽ የተደረገው ገንዘብ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን የጉምሩክ መ/ቤት ዲሬክተር በሚመለከተው ግለሰብ ላይ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ጥያቄ (ክስ) ማቅረብ አለበት። ይህ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው በዕቃዎቹ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ልክ ያነሰ ቀረጥ ከተከፈለበት ወይም ግብር ከፋዩ በስሕተት ተመላሽ ገንዘብ እንዲወስድ ከተደረገበት ቀን እንስቶ ነው።

በተፈጸመው ስሕተት ተጠቃሚ የሆነው ግለሰብ በልዩነት የሚፈለግበትን ቀረጥ ወይንም እንዲወስድ የተደረገውን ተመላሽ ገንዘብ ለመንግሥት የመክፈል ወይም ገቢ የማድረግ ሕጋዊ ግዴታ የሚኖርበት የጉምሩክ መ/ቤት ዲሬክተር በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ጥያቄ (ክስ) እስከቀረበ ድረስ በመሆኑ ጊዜው ካለፈ በኋላ ጥያቄው (ክሱ) ሊቀርብ አይችልም።[24]

ሁለተኛው ምሳሌ ከገቢ ግብር አወሳሰን ጋር የተዛመደ ሲሆን ለዚህ ጽሁፍ ጥናት ይበልጥ የቀረበ ነው። አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ አንድ ግብር ከፋይ የገቢውን መግለጫ ካቀረበበት ቀን አንስቶ በአለው የ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ የገቢ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የሚፈለግበትን ግብር አጠናቆ የመወሰን ሕጋዊ ግዴታ አለበት። ይህ የጊዜ ገደብ ካለፈ መ/ቤቱ የገቢ መግለጫ ለቀረበለት የግብር ዘመን የዓመቱን ግብር የሚከፈልበት ገቢ የመወሰን መብቱን ያጣል። የተገለጸውም ገቢ ተቀባይነት እንዳለው (እንደጸደቀ) እና ግብሩም በዚሁ ላይ እንደተወሰነ ይቆጠራል። ስለሆነም ይህ ግብር ከፋዩ በገቢ መግለጫው ላይ ሳይገልጸው በቀረው ገቢ ላይ ለሚፈለገው ግብር ያለበትን ኃላፊነት አያስቀርለትም።[25]

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) የጊዜ ገደብ የተደነገገበት ጉዳይ ይህ ብቻ ነው። ታዲያ ከዚህ በመነሳት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሌላ ማናቸውም ሁኔታ ግብርን ለመሰብሰብ ያለው የመክሰስ መብት በጊዜው ያልተወሰነና ቀሪ ሊሆን የማይችል ነው ማለት ይቻላልን? በተከታዩ ክፍል መፍትሄ (ምላሽ) ለመስጠት የሚሞከረው ለዚህ ጥያቄ ነው።

## 2. የፍትሐ ብሄር ሕግ ያለው አግባብነት

በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ሕግ ለ4ኛው መጽሐፍ የተሰጠው ርዕስ (ስለግዴታዎች) የሚል ነው። በሥሩ በመጀመሪያ የሚመጣው ስለውሎች በጠቅላላው በተሰኘ ርዕስ 12ኛው አንቀጽ ነው። የዚህ አንቀጽ 3ኛ ምዕራፍ በስድስተኛው ክፍል ይርጋን የሚመለከቱ 12 ቁጥሮች ይደረድራል።[26] ተከታዩ ተግባር እንግዲህ ይህ የፍትሐብሄር ክፍል ግብርን ለሚመለከቱ ክሶች ያለውን አግባብነት መመርመር ይሆናል።

ትንታኔው በዋናነት የሚያተኩረው በቁጥር 1677 እና በቁጥር 1845 ድንጋጌዎች ላይ ነው። ይህም የሆነው አከራካሪ በመሆናቸው ነው። የመጀመሪያው መሠረታዊ የሆነውን የአንቀጽ 12ትን የአፈጻጸም አድማስ የመወሰን ጥያቄን ያስነሳል።[27] ሁለተኛው ደግሞ በስሩ የተደነገገው የ10 ዓመት ይርጋ ልዩ ባሕሪ ያለው ማለትም አግባብነቱ ለውሎች ብቻ ነው ወይንስ አጠቃላይ ባሕሪ ያለው ማለትም ምንጩ ምንም ይሁን ምን በማናቸውም ግዴታ ላይ ተፈጻሚ ነው የሚለውን ጭብጥ ያስነሳል።[28] ይሁንና በማስቀደም የግብር ሃላፊነት (ዕዳ) ራሱ ግዴታ መሆኑን ማብራራት አስፈላጊም ሆኖ ይገኛል። ምክንያቱም መላው ትንታኔ ይህንን ነጥብ መሠረት ያደረገ በመሆኑ ነው።

ግዴታ ለሚለው ቃል የተለያዩ ትርጉሞች ተሰጥተው ይገኛሉ። ሆኖም በራውሊ አንጓለለ ክላሲካዊ ትርጉሙ "በሀገራችን ሕጎች መሠረት አንድን ነገር እንድንፈጽም አስፈላጊነቱ አስገዳጅ የሚሆንብን ሕጋዊ ማሰሪያ።[29] ... አንድን ተግባር በመፈጸም ወይም ባለመፈጸም የሚገለጥ በሕግ የተጣለ ጫና..." ነው። በአሁኑ ጊዜ የግዴታ ጽንሰ ሐሳብ በገንዘብ ጠያቂና በባለዕዳ መካከል ያለውን ሕጋዊ ግንኙነት ሁሉ ይመለከታል፤

የሚለው አስተሳሰብ በሰፊው ተቀባይነት አያገኘ ነው። የዚህም ግንኙነት መሠረታዊ ባሕሪያት መብትና በአንጻሩ ያለው ግዴታ (Duty) ነው።[30]

በቀ ባለ አገላለጽ ከስር አመጣጣቸውን መሠረት በማድረግ ግዴታዎች የውልና የውል ያልሆኑ ተብለው ሊመደቡ ይችላሉ። የውል ግዴታዎች ተዋዋይ ወገኖች ወደው በሚያደርጉት ስምምነቶች የሚፈጠሩ ናቸው። የውል ያልሆኑ ግዴታዎች ደግሞ የሥር አመጣጣቸው አንድም ግለሰቦች በሚፈጽሟቸው በሕግ የተፈቀዱ ወይም ገደብ የተደረገባቸው ተግባሮች ወይም ከሕጉ ከራሱ ሥልጣን ነው።[31]

በሕግ ምሁራን አካባቢ የግዴታ ጽንሰ ሐሳቦችን በግል ሕግ ይልቁንም በውል ሕግ አግባብ ማብራራት ተቀባይነትን አግኝቶ የቆየና የተለመደ ነው። ይህ አቀራረብ ግን ግዴታዎች የሕዝብ ሕጎች ካላቸው ሥልጣንም የሚመነጩ መሆኑን ሊያጠራጥር አይገባም። ግብሮች እንዲከፈሉ ግዴታዎችን የሚጥሉ የገቢ ሕጎች ለዚህ ዓይነተኛ ምሣሌ ናቸው።

ግዴታዎች በባሕሪያቸው ወደ ፍትሐብሔር እንጂ ወደ ወንጀል ክስ የሚያመሩ አይደሉም። ስለዚህ እንደደንቡ የግብር አላፊነት የሚያመራው ወደ ፍትሐብሔር ክስ ነው። ያም ሆኖ የገቢ ሕጎች ብዙውን ጊዜ አልማጭ በሆኑ ግብር ከፋዮች ላይ በተጨማሪ የወንጀል ክስ ሊቀርብ ስለመቻሉ ይደነግጋሉ።[32] ይህ የሆነበት ምክንያት በግብር ጉዳዮች ያለው የሕዝብ ጥቅም አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ስጋት ስላለ ነው።

ይሁን እንጂ የፍትሐብሔርና የወንጀል ክሶች ሊቀርቡ የመቻላቸው ሁኔታ መጣመሩ የግብር ኃላፊነትን እንደ አንዱ የግዴታ ዓይነት አድርጎ ለመረዳት የሚያውክ ብዥታ መፍጠር አይኖርበትም። ምክንያቱም ከሁለቱ እያንዳንዱ አማራጭ ራሱን የቻለና የሌላው ጥገኛ ስላልሆነ ነው።[33]

የግብር ኃላፊነት በገንዘብ ጠያቂና በባለዕዳ መካከል በውል ከሚፈጠሩት ሕጋዊ ግንኙነት ጋር እጅግ የሚመሳሰሉ ግንኙነቶች የሚታዩበት ነው።

በቀም ትርጉሙ ግብር ዕዳ ነው ማለት ፍች የለሽ መሆኑ አይካድም፣ ምክንያቱም በአስፈላጊነት ላይ የተመሠረተውን የማስገበር ሥልጣን ሕግ አውጭው በመጠቀሙ በግድ ያሚሰበሰብ መዋጮ ስለሆነ ነው።[34] እንዲሁም በመሆኑ፣ ለምሳሌ የማቻቻል ሥርዓት አይፈጸምበትም።[35] ሆኖም የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከግብር ከፋዩ አንጻር ያለው አቋም በውል አንዱ ተገዛቢ ወገኑ ከባለዕዳው አንጻር ከሚኖረው አቋም ጋር ከሞላ ጎደል አንድ ዓይነት ነው። ሁለቱም ያላቸው ተለይቶ በታወቀ ሰው ወይም ተለይተው በታወቁ ሰዎች ወይም በተወሰኑ የሰዎች መደብ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል ስለሆነ መብት (Right in Personam) ነው። በመሠረቱ እነዚህ ያሉት ግዴታዎች ግዴታ ለተገባለት ሰው የባለግዴታውን ተግባሮች ሁሉ ለመቆጣጠር የሚያስችል መብት እንዲፈጥሩ የታቀዱ አይደሉም። ባለዕዳው ያለበትን ዕዳ ለመክፈል ከንብረቱ ከፊሉን በመስጠት ከገባበት የውል ግዴታ ነጻ ለመሆን እንደሚችል ሁሉ ግብር ከፋዩም እንዲሁ የግብር ዕዳውን ለመክፈል ከንብረቱ ከፊሉን በመስጠት ካለበት የግብር ኃላፊነት ነጻ ሊሆን ይችላል።

ልዩ ድንጋጌዎች እስከሌሉ ድረስ ከውል ያልመነጩ ቢሆንም እንኳ አግባብ ያላቸው የዚህ አንቀጽ ቁጥሮች በግዴታዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆኑ በቁጥር 1677 ተገልጿል። ይህ ማለት ሕግ አውጭው እነዚህን ግዴታዎች የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች ከደነገገ እነዚህ ድንጋጌዎች በአንቀጽ 12 ባሉት ቁጥሮች ላይ የበላይነት ይኖራቸዋል። በተቃራኒው ልዩ ድንጋጌዎች በሌሉበት ሁኔታ የዚህ አንቀጽ ቁጥሮች አግባብነት እስካላቸው ጊዜ ድረስ የውል ካልሆኑ ግዴታዎች የሚነሳ አንድ ችግርን ለመፍታት ያገለግላሉ።

የዚህ ቁጥር ቋንቋ የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ ከውል ጉዳዮች ድንበር ያለፈ መሆኑን ያለምንም ጥርጥር ያረጋግጣል። አግባብ ያላቸው የአንቀጹን ድንጋጌዎች በፍትሐብሄር ውስጥ ለተመለከቱ ከሥር አመጣጣቸው ከውል ላልሆኑ ግዴታዎች ተፈጻሚ ማድረግ የሚቻል መሆኑ አያጠያይቅም። አከራካሪው ጥያቄ ግን የአንቀጹ የአፈጻጸም አድስ የተዘረጋው ምንም ልዩነት ሳይደረግ የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን ሁሉ እንዲመለከት ለማድረግ ታቅዶ ነውን? የሚለው ነው።

ሕግ አውጭው "ስለ ውሎች በጠቅላላው" የሚለው አንቀጽ ያለውን የአፈጻጸም አድማስ እንዲሰፋ ያደረገው አግባብ ያላቸው የአንቀጹ ድንጋጌዎች በፍትሐ ብሄር ውስጥ በሚገኙ እንደ status ውርስ፣ ከውል ውጭ የሆነ ኃላፊነት፣ አለአግባብ መበልጸግ ካሉ ሕጎች በሚመነጩ የውል ያልሆኑ ግዴታዎች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆኑ በማቀድ ነው የሚል አመለካከት ሊኖር ይችላል። ይህንንም ለመደገፍ ሕጉን ያረቀቁት ኤክስፐርት በቁጥር 1677 ሥር ያሰፈሩትንና ከዚህ በታች የተጠቀሰውን ማብራሪያ መጥቀስና በማብራሪያው ውስጥ እንደቃሉ አጠቃቀም ሕግ የሚለው ቃል የሚመለከተው ፍትሐብሄር ነው በማለት መከራከር ይቻላል።

"ግዴታዎች ሕጉ ራሱ እና ግለሰቦች የሚያደርጓቸው ውሎች የሚፈጥሯቸው ናቸው። ይሁንና በነዚህ የተለያዩ ምንጮች መካከል መሠረታዊ የሆነ ተቃርኖ የለም ስል ባለው አመለካከት ውሎች የሚኖራቸው የአስገዳጅነት ኃይል እንኳ አመሠራረታቸውን በሚገዛው እና ተፈጻሚነታቸውን በሚያረጋግጠው ሕግ ላይ የተደገፈ ነው። በተጨማሪ ተዋዋይ ወገኖች የሚያደርጓቸውን ስምምነቶች ብዙውን ጊዜ ሕጉ ያሟላል። የውሉ ይዘት ምን ዓይነት መሆን እንዳለበት ከመወሰኑ በፊት ተዋዋይ ወገኖች ስምምነታቸውን በሚያደርጉበት ጊዜ አስቀድመው ይደርሳሉ ብለው ሳይገምቷቸው ሆኖም ከዚያ በኋላ ሊነሱ ለሚችሉ በርካታ የተለያዩ ችግሮች መፍትሄዎችን ይደነግጋል። በመጨረሻም ሕግ አውጭው ፍትሀን ማስፈንና የህብተረሰብ ጥቅም እንዲጠበቅ ማድረግ ስላለበት አንዳንድ አዛዥነት ያላቸውን ድንጋጌዎች እንዲኖሩ አድርጓል"።[36]

ከፍ ብሎ በሰፈረው ጥቅስ አግባብ ሕግ የሚለው ቃል ለፍትሐብሄር ሕግ ምትክ ሆኖ የቀረበ መስሎ ይታያል። ምክንያቱም ቃሉ የተጠቀሰው ከውል ጋር በተገናኘ መልኩ ስለሆነ ነው።[37]

ወደ ሕጉ ሲኬድ በቁጥር 1676 እና በቁጥር 1677 መካከል የሚደረግ ማነጻጸር ለችግሩ መፍትሄ እንደሚያስገኝ ይገመታል። እነሱም በዛም ሁለቱ ድንጋጌዎች ተመሳሳይነት ባለው ቋንቋ የተቀረፁ ሲሆኑ "ስለውሎች በጠቅላላው" የሚለው አንቀጽ ያለው የአፈጻጸም አድማስ ከአንቀጹ መደበኛ ክልል አልፎ የተዘረጋ መሆኑን ይገልጻሉ። ያላቸው መሠረታዊ ልዩነት የመጀመሪያው ውሎችን በሚመለከት የሚናገር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን በሚመለከት የሚናገር መሆኑ ነው።

ቁጥር 1676 የአንቀጽ 12 ድንጋጌዎች የተዋዋይ ወገኖችን ማንነት ወይም የውሉን ዓይነት መሠረት በማድረግ ምንም ልዩነት ሳይፈጠር በሁሉም ውሎች ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታ ይገልጻል። ይሁንና ከቁጥር 1777 ድንጋጌ በተለየ አኳኋን በስእንዳንድ የውል ዓይነቶች የተደነገጉ ደንቦች በሕጉ ውስጥ የት እንደሚገኙ በግልጽ ያመለክታል። እነዚህም የፍትሐብሄር ሕግ 5ኛ መጽሐፍና የንግድ ሕግ በመባል ተጠቅሰዋል።[38] ቁጥር 1677 ይህን አያደርግም በመሆኑም ይህን ሳያደርግ የቀረበትን በምክንያት የተደገፈ ማብራሪያ መኘት አግባብ ይሆናል። ሕግ አውጭው ቁጥር 1677ትን ሲደነግግ ሳያጣቅስ የተወው ሆን ብሎ ሳይሆን በመዘንጋት በስሆነ የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ የተዘረጋው በፍትሐብሄር ሕጉ ውስጥ ያሉትን የውል ያልሆኑ ግዴታዎች ብቻ እንዲሸፍን ታቅዶ ነው ማለት ይቻላል። ይሁንና የነዚህ ድንጋጌዎች ቁጥሮች ተከታታይ መሆን እንዲህ ዓይነቱን አመለካከት ትርጉም የለሽ ሊያደርገው ይችላል። ሕግ አውጭው በአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ ላይ እንዲህ ያለውን ገደብ ማበጀት አቅዶ ቢሆን ኖሮ በደንቦች ሲደነግግ እንዳደረገው ሁሉ በቁጥር 1677ትም የውል ያልሆኑ ግዴታዎች የት የት እንደሚገኙ በእርግጥ ማመልከት ባላቃተው ነበር።

ስለዚህ ሳያጣቅስ የተወው ሆን ብሎ ነው። ዓላማውም የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ መላውን የፍት/ብሄር ሕግ እንዲመለከት ማድረግ ነው።

የአንቀጹ አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ከፍ/ብሄር ክልል አልፎ የሚሄድ ሊሆን ግዴታዎችን በሚፈጥሩ ሕጎች ውስጥ የሚያጋጥሙ ክፍተቶችን የመሙላት ሚና እንዲኖራቸው የታቀዱ ናቸው። የግብር ህጎች የፊስካል ግዴታዎች ምንጭ እንደመሆናቸውም በዚህ ረገድ የተለዩ ሆነው አይታዩም።

በታሪክ የኢትዮጵያ የፍ/ብሄር ሕግ አውቶሪቲ በመባል ሊታወቁ የሚችሉት ፕሮፌሰር ጆርጅ ቹቹ ኖቪጆ ስለ አንቀጽ 12 ባቀረቡት ትችት መግቢያ ላይ ስለዚህ ነጥብ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ገልጸዋል ይህም ቀጥሎ ቃል በቃል እንዳለ ቀርቧል።

"በጀርመን የፍ/ብሄር ሕግ ከማናቸውም ምንጭ የተገኙ ግዴታዎችን የሚገዙ ደንቦች ከውል ሕግ ቀድመው ይገኛሉ። ኢትዮጵያዊው ሕግ አውጭ ተቃራኒውን ቴክኒክ

ተጠቅሟል። የግዴታዎች ዋነኛ መንስኤ በሆነው በውል ይጀምራል። ይሁንና "ስለውሎች በጠቅላላው" የተጻፈው ሕግ በቁጥር 1677 እንደተመለከተው አግባብነት እስካለው ድረስ ከማናቸውም ምንጭ በተገኙ ግዴታዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል"[39]

ደራሲ በቁጥር 1677 ስር ባቀረቡት ትችት በዚህ ነጥብ ላይ ያላቸው አቋም ፍጹም የማያወላውል መሆኑን አሳይተዋል። እዚህ ላይ (ስለ ውሎች በጠቅላላው) በሚለው አንቀጽ የታቀፉት ድንጋጌዎች ከየትም በመነጩ ግዴታዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ሊሆኑ ስለሚችሉበት ሁኔታ ብቻ አጠናክረው በመናገር አልተወሰኑም። ከዚሁ ጋር ጉዳዩ በሚመለከተው የግል ወይም የሕዝብ ሕግ ዘርፍ ለሚያጋጥም ፍትሐብሄራዊ ባሕሪ ያለው ማናቸውም ችግር መፍትሄ ማግኘት ባልተቻለ ጊዜ ሁሉ ለመፍትሄው አንቀጽ 12 ውስጥ ወዳሉት ድንጋጌዎች መመለስ የተፈቀደ መሆኑን በአፅንኦት ገልጸዋል። አነጋገራቸው ከፍተኛ የማስተማርና የማሳወቅ ፋይዳ አለው።

"የግዴታዎች ሕግ ለሁሉም የግል ሕግና የሕዝብ (መንግሥት) ሕግ እንኳ ሳይቀር ለምሣሌ የፊስካል ግዴታዎች ታዕታይ የሕግ ምንጭ ነው። ስለዚህ ስለውሎች በጠቅላላው የሚለው አንቀጽ ውሎችን ብቻ ሳይሆን ሁሉን ግዴታዎች የሚመለከቱ የውል ድንጋጌዎች የሚገኙበት በመሆኑ ያለው ዋጋ እጅግ ከፍተኛ ሆኖ ይገኛል። የግዴታዎች ሕጉን በተመለከተ ብቻ ሳይሆን፣ ተገቢውን ተግባራዊ በማድረግ በሌሎችም የግል ሕግ መስኮች አጠራጣሪ ሲሆን ላጋጠመው ችግር መፍትሄ ለማግኘት ተመልሶ የምናየው አግባብነት እስካላቸው ድረስ እነዚህ ድንጋጌዎችን ነው። እንዲሁ ያለው ታዕታይ ወደሆነው ሕግ ተመልሶ በማመሳሰል የትርጉም ዘዴ መጠቀም በፍትሐብሄር የተከለከለ አይደለም። በተቃራኒው በማመሳሰል መተርጎም በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁጥር 2 በግልጽ ተከልክሏል።"[42]

ከዚህ በላይ አንቀጽ 12 የተዘረጋበትን የአፈጻጸም አድማስ በሚመለከት የተነሳው ጥብቅ ምላሽ እንዳገኘ ይገመታል። ይሁንና በአንቀጽ 1677 ውስጥ (Relevant) "አግባብ ያላቸው" ስለሚለው አባባል በአጭሩም ቢሆን መግለጽ አስፈላጊ ይሆናል። በአንቀጽ 12 ውስጥ ካሉት ድንጋጌዎች አንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ የውል ባሕሪ ያላቸው እንደሆኑ መገንዘብ ያሻል። እንግዲህ የውል ካልሆኑ ግዴታዎች ጋር ጨርሶ ሊጣመሩ የማ

ይቸሉ ድንጋጌዎች የሚኖሩቸው አፈጻጸም በውል ሕግ ከሌሌ የተወሰነ ነው። በእንቀጽ 12 ካሉት ድንጋጌዎች መካከል የትኞቹ ሙሉ በሙሉ የውል ባሕሪ ያላቸው እንደሆነ መለየት የሚቻለው አእምሮን በመጠቀም ሊሆን በቁጥር 1677 ድንጋጌ ውስጥ የሰፈረው Relevant (አግባብ ያላቸው) የሚለው ቅጽል ይህንኑ ነጥብ የሚጠቁም ነው። አሁንም ለአንድ ጊዜ ፕሮፌሰር ቭቻ ናዚች የውል ላልሆኑ ግዴታዎች አግባብነት ሊኖሩቸው ስለሚችሉት ድንጋጌዎች የጻፉትን መጥቀሱ ጠቃሚ ይሆናል።

> "Relevant (አግባብነት ያላቸው) የሚለው አቀባዊ ገላጭ ከነጋገር ያግባብነትን የሎጂክ ደንቦች ወይም በቀላሉ አገላለጽ ተራ የውል እውቀትን መሠረት በማድረግ ሊታዩ የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን የማይመለከቱ ለምሳሌ በምዕራፍ 1 ስለውል አመሠራረት የሚናገሩትን ድንጋጌዎች ከአፈጻጸም ውጭ የሚያደርግ ነው። በሌላ በኩል በምዕራፍ 2 ስለ ውሎች አፈጻጸምና ውልን ባለመፈጸም ከሰፈሩት ደንቦች እንዳንዶቹ እንዳግባብነታቸው የውል ባልሆኑ ግዴታዎች መፈጸም ወይም አለመፈጸም ተፈጻሚነት ይኖሩቸዋል። በምዕራፍ 3 እዳዎችን በመግር፣ በመተካት፣ በማቻቻል፣ በመቀላቀልና በደርጋ ስለ ግዴታዎች መቅረት የተደነገጉት ደንቦች የውል ባልሆኑ ግዴታዎች መቅረት ላይ በሚገባ ተፈጻሚ ይሆናሉ።"[41]

ከፍ ብሎ የሠፈረው ጥቅስ በቁጥር 1677 አጠቃቀም ሬለቫንት (አግባብነት ያላቸው) የሚለውን አቀባዊ ገላጭ ሀረግ መረዳት የሚገባው እንዴት እንደሆነ የሚያብራራ ብቻ ሳይሆን ከዚህ ትንታኔ መነሻ ላይ በተነሳው ቀና ጥያቄ አውንታዊ የሆነ ምላሽ የሰጠ ነው። ጉዳዩን የሚመለከቱ ልዩ ድንጋጌዎች እስከ ሌሉ ድረስ የፍትሐብሔሩን የእንቀጽ 12 አግባብነት ያላቸው የደርጋ ድንጋጌዎች በግብር ነክ ክሶች ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ ስሕተት እንዳልሆነም ያረጋግጣል።

ይህ እስከሆነ ድረስ የቁጥር 1845 ድንጋጌን አስመልክቶ በተነሳው ጭብጥ ላይ መተቸት ፋይዳ ያለው መስሎ አይታይም። በእርግጥም ቁጥር 1845 የሚናገረው ስለ ውል መሆኑ ማብራሪያ የሚሻ አይደለም። "ስለ ውሎች በጠቅላላው" በሚለው እንቀጽ ስር ያለው እያንዳንዱ ቁጥር የሚናገረው ስለ ውል በመሆኑ በዚህ ቁጥር ላይ ትችት ሊቀርብ ያስፈለገበትም ምክንያት ይህ ሊሆን አይችልም። ትንታኔው የቀረበው የቁጥር

1845 ድንጋጌን አፈጻጸም በውሎች ላይ ብቻ የመወሰን ዝንባሌ ይኖራል በሚል ፍራቻ ነው።

> "ቁጥር 1845 የሚመለከተው ከሥር አመጣጣቸው ከውል የሆኑ መብቶችን ነው። ሆኖም ስለ ይርጋ የሚወሰኑ ደንቦች ሌሎች ችግሮችን ለመፍታት የሚያገለግሉ መሆናቸው አያጠራጥርም። በንብረትና በቤተሰብ ሕግ ዘርፎች የይርጋ አስፈላጊነት ሲጤን እንምርት ውስጥ ከሚገቡት ነጥቦች ጋር አንድ ዓይነት ላይሆን ይችላሉ። ይህ እውነታ የቁጥር 1845 ድንጋጌ አፈጻጸም እንዲጠብ የተደረገው በአግባቡ እንደሆነ ያመለክታል።"[42]

ይህ ከላይ የሰፈረው ጥቅስ በቁጥር 1845 ስር የተደነገገው የ10 ዓመት ይርጋ ልዩ ባሕሪ ያለው ማለትም ከውል የመነጩ ግዴታዎችን ብቻ የሚመለከት ነው፤ የሚለውን ክርክር የሚደግፍ ሆኖ ሊታይ ይችላል። ሆኖም ስለውሎች በጠቅላላው የሚለው አንቀጽ ካለው አጠቃላይ መሠረታዊ የሆነ ዓላማ አንጻር ሲታይ፥ ይህ አመለካከት ተቀባይነት እንደማይኖረው በቀላሉ መገንዘብ ይቻላል።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በቁጥር 1677 የአንቀጽ 12 የአፈጻጸም አድማስ የተዘረጋው ሕግ አውጭው በግዴታዎች ሁሉ ላይ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ በመፍጠር በቀሪው የግል ሕግ ውስጥ የሚመለከተው ድንጋጌ ያልተገኘለትን ማናቸውንም ችግር ለመፍታት እንዲቻል ባለው እቅድ ነው። ከዚሁ ጋርም በዚህ አንቀጽ ሥር የሚገኝ አንድ ድንጋጌ እንዲህ ባሉ ሁኔታዎች ላይ ተፈጻሚ መሆን ወይም አለመሆኑ መወሰን ያለበት በሎጂክ የአግባብነት ደንቦች መሠረት ብቻ መሆን እንዳለበት በሚገባ ተገልጿል። ስለዚህ ቁጥር 1745 አግባብነት የለውም በሚል ካልሆነ በቀር በማናቸውም ሌላ ክምንያት ያለውን ተፈጻሚነት በውሎች ላይ ብቻ እንዲሆን አድርጎ ማጥበብ አንቀጹ ካለው መሠረታዊ ዓላማ እንደሚፈንገጥ ሆኖ ይቆጠራል።

ቁጥር 1845 የሰር አመጣጣቸው ከውል ላልሆኑ ግዴታዎች መፈጸም ለሚቀርበው ክስ አግባብነት አለውን? የሚለው ጥያቄ ሲታይ መልሱ አውንታዊ እንደሆነ ወዲያውኑ ግልጽ ይሆናል። ድንጋጌው የተቀረፀበት ቋንቋ ያኸውን ያህል ጠባብ ሆኖ ቢታይም የውል

ባሕሪ ብቻ ያለው ነው የሚያሰኝ እንዳች ነገር የለም። የ10 ዓመት ይርጋውንም ለዚ ድንጋጌ ያልተደነገገለት የስር አመጣጡ ውል ላልሆነ ግዴታ መፈጸም በሚቀርቡ የክስ መብቶች ላይ ተፈጻሚነት እንዲኖረው ማድረግ ከቶውኑ ሎጂክን የሚጻረር አይሆንም ምናልባት ይህ የ10 ዓመት ይርጋ ከውል ጋር ጨርሶ ግንኙነት የሌለውን አንድ የይርጋ ጥያቄ ለመፍታት የሚጠቅም መሆኑን ለማሳየት ከአንድ ምሁር ሥራ ምሣሌ መጥቀስ ተገቢ ይሆናል።

"የፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ለፍርዱ አፈጻጸም መቅረብ ያለበት የመጀመሪያ ማመልከቻ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መሆን እንደሚገባው አይደነግግም። የተሰጠው ፍርድ ለፍርድ ባለመብቱ ጥቅም ይሁን ግዴታ የሚጥል በመሆኑ ግዴታዎችን ለማስፈጸም ስለሚቀርበው ክስ የተደነገገው የተለመደው የ10 ዓመት ይርጋ ተፈጻሚ ሊሆንበት ይገባል። በመሆኑም ፍርድ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ ከ10 ዓመት በኋላ ለአፈጻጸም የሚቀርብ ማመልከቻ በይርጋ መከልከል ይኖርበታል።"[43]

ይህ ከሆነ እንግዲህ ቀደም ሲል የተጠቀሰውን የኤክስፐርት አርቃቂውን አነጋገር በምን መልኩ መረዳት ይገባል? ፕሮፌሰር ሬኔ ዴቪድ ስለቁጥር 1845 ሲተቹ (ሲያብራሩ) በሌሎች ሀገሮች የሕግ ሥርዓቶች ያላቸውን የይርጋ ድንጋጌዎች በመጥቀስ ያላቸውን አርዝማኔ በዚህ ቁጥር ሥር ከተመለከተው የ10 ዓመት ይርጋ ጋር አነጻጽረዋል። ይህንንም ሲያደርጉ ይርጋ ከ10 ዓመት በላይ የሆነ ጊዜ ሊኖረው የማይደግፉ መሆናቸውን አልሸሸጉም። እንዲህ ይላሉ፡

"የፈረንሳይ የፍትሐብሄር ሕግ ቁጥር 2262 (መልሶ መውሰድ) የማይቻልበትን ጊዜ ከ30 ዓመት በኋላ እንዲሆን ደንግጓል። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ እጅግ ረጅም መሆኑን ሁሉም ይስማማበታል። ከዚህ ሌላ እንደ የስዊዘርላንድ የግዴታዎች ሕግ በቁጥር 1277፣ የጃፓን በቁጥር 167፣ የሊባኖስ በቁጥር 347፣ የኢጣሊያ በቁጥር 2946 እንደሚያደርጉት ሁሉ ቁጥር 1845 የ10 ዓመት ይርጋ ደንግጓል።[44] ምንም ይህ ቢሆን እንኳ በኢትዮጵያ የፍትሐብሄር ኮድ የንብረትና የቤተሰብ ሕግ መስኮች ከዚህ የረዘመ ይርጋ የሚደነግጉ አንዳንድ ቁጥሮች ይገኛሉ።"[45]

ከዚህ አንጻር ስለ ቁጥር 1845 አፈጻጸም የጸሐፊን መረዳት የሚገባው ከፍትሐብሔር ሕግ ከ10 ዓመት በላይ የሆነ ይርጋ ከሚደነግጉት ድንጋጌዎች አኳያ ነው። አነጋገሩ የስር አመጣጣቸው የውል ያልሆኑ ግዴታዎችን ሁሉ የቁጥሩ ድንጋጌ ካለው የተፈጻሚነት ክልል ውጭ እንዲያደርጋቸው ሆኖ መወሰድ አይኖርበትም።

ለማጠቃለል በቁጥር 1845 ስር የተመለከተው የ10 ዓመት ይርጋ አጠቃላይ ባህሪ ያለው ነው። በመሆኑም ልዩ የይርጋ ድንጋጌዎች እስከሌሉ ድረስ ከየትኛውም ምንጭ የተገኙ ግዴታዎችንም ግዴታ በሚመለከቱ የክስ መብቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። እንዲሁ እንደ መሆኑ ግብር ከፋዮች በፍትሐብሔር ሥነ ሥርዓት ሕግ ቁጥር 244 (2) መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በማድረግ ዋጋ ያለው የይርጋ መከላከያ ሊያነሱና በሕግ በተፈቀደው ጊዜ ውስጥ ያልቀረቡትን ግብር ነክ ክሶች ውድቅ እልባ ለማድረግ ሊጠቀሙበት ይችላሉ።

3. <u>ስለአፈጻጸም የቀረቡት ሃሳቦች</u>

ከእንግዲህ የቀረው ተግባር የተለያዩ ሁኔታዎችን በመውሰድ በሰንጠረዥ 'ሐ' ከተመለከቱ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ የተጣለውንም ግብር ለመሰብሰብ በሚቀርቡ ክሶች ጋር የተያያዙ የይርጋ ጥያቄዎች እንዴት መወሰን እንዳለባቸው ለማሳየት መሞከር ይሆናል።[46] ይህ የዚህ ጽሁፍ ክፍል ለዚህ ተግባር እንዲውል የታቀደው የገቢ ግብር ሕጎችን ሥራ ላይ የማዋልና የማስፈጸም ኃላፊነት ላለባቸው እንዲሁም በተግባር የሚነሱ ጥያቄዎች ሊኖረው እንደሚችል ተስፋ በመደረጉ ነው።

1. <u>አንድ ግብር ከፋይ ዓመታዊ የገቢ መግለጫውን ሳያቀርብና በዚሁ ላይ ግብር ሳይከፍል የቀረበት ሁኔታ፥</u>

በሠንጠረዥ 'ሐ' ከተመለከቱ ምንጮች በተገኘ ገቢ ላይ ተከፋይ ለሚሆነው ግብር ያለው ኃላፊነት የሚወሰነው ዓመትን መሠረት በማድረግ ነው። ግብር ከፋዮች ሁሉ በያንዳንዱ የግብር ዘመን መጨረሻ ዓመታዊ የገቢ መግለጫቸውን እንዲያቀርቡና በዚሁ

ላይ የሚፈለገውን ግብር እንዲከፍሉ ግዴታ ተጥሎባቸዋል።[47] ታዲያ አንድ ግብር ከፋይ አንድን የግብር ዘመን በሚመለከት እነዚህን ግዴታዎች እንዳልፈጸመ ሲገመት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በግብሩ ላይ ያሉትን መብቶች ሥራ ላይ በማዋል ረገድ የይርጋ ክርክር ሲቀርብበት በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ሊሰጥበት ይገባልን?[48] ከዚህ በታች ለማየት እንደሚሞከረው የዚህ ዓይነቱ ጉዳይ አወሳሰን ውስብስብ ነው።

አሁን በመተቸት ላይ ያለውን ሁኔታ የሚመለከቱ ልዩ የይርጋ ድንጋጌዎች የሉም። ስለዚህ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ሥር የሚገኘው አጠቃላይ ይርጋ ፊሉን ያለ ማለት ነው። በመሆኑም አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለው ግብር የመወሰንና የመሰብሰብ መብቶች 10 ዓመት ካለፈ በኋላ ሥራ ላይ እንዳይውሉ የተከለከሉ ይሆናሉ ማለት ነው። የቀረበበትን ክስ ውጤት አልባ ለማድረግ ግብር ከፋዩ የይርጋ መከላከያ ያነሳ ከሆነ አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ማናቸውም በግብር ይርጋው ሳይቋረጥ ካለፈ በኋላ በተደረገና የግብር ውሣኔ መሠረት ሊሰበሰብ አይችልም።

የግብር ከፋዩ ማንነት ወይንም የሥራና የመኖሪያ ቦታው በግብር ባለሥልጣኑ መ/ቤት ዘንድ ባልታወቀበትና የይርጋው ማለፍም ምክንያት ይህ ሆኖ በተገኘበት ሁኔታ ከፍ ብሎ የቀረበው የአፈጻጸም አሳብ አጠያያቂ ይሆናል። ሕጉ አሁን ባለበት መልክ የሚነሳውን የይርጋ መከላከያ የዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ባለመኖሩ ምክንያት ውድቅ ለማድረግ ይፈቅዳልን? የሚለውን ጥያቄ መመርመር ያሻል።

የሐብትነት መብት ሥራ ላይ ሳይውል የጊዜ ገደብ በማለፉ ቀሪ የሚሆንበትን ሁኔታ በሚመለከት ስለመብቱ መኖር አለማወቅ የሚነሳውን የይርጋ መከላከያ በቂ ሕጋዊ ምክንያት አለመሆኑ ተመልክቷል።[49] ስለ ውሎች በጠቅላላው ለሚለው አንቀጽ በ3ኛው ምዕራፍ በስድስተኛው ክፍል ውስጥ ግን ይህን የመሰለ ድንጋጌ አይገኝም፤ ይሁን እንጂ ከላይ የተጠቀሰውን የይርጋ ደንብ በማመሳሰል የአተረጓጎም ዘይቤ ከግዴታዎች ጋር የተያያዙ መብቶችን ለማስቀረት ታቅደው ለተደነገጉ ይርጋዎችም አግባብነት እንዳለው መመልከት የተከለከለ አይደለም።

ከዚህ በተጨማሪ የፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1853 ሕግ አውጭው የይርጋ መከላከያን ውድቅ የሚያደርጉ ምክንያቶች እንዴት ያሉት ናቸው? ለሚለው ጥያቄ ትኩረት ሳይሰጥ እንዳሳለፈ የሚያሳይ መሆኑን መረዳት ያቻላል። ሕግ አውጭው መከላከያው ስለማያገለግልባቸው ሁኔታዎች ሲደነግግ የመብት መኖር አለማወቅን አልጠቀሰም።[50]

በመጨረሻ የይርጋ መከላከያ ቅን ልቡና በሌለው ተከሣሽ እንኳ ሊነሳ እንደሚችል በቁጥር 1854 የተመለከተ መሆኑን መገንዘብ ይገባል።[51] እንግዲህ ከፍ ብሎ በተገለጹት ምክንያቶች ምንም እንኳ ይርጋው ሊያልፍ የቻለው መ/ቤቱ የግብር ከፋዩን ማንነት ወይም የሥራና የመኖሪያ አድራሻ ሳያውቅ በመቅረቱ የተነሳ ቢሆን ግብር ከፋዩን የይርጋው ተጠቃሚ እንዳይሆን ለመከልከል ሕጋዊ መሠረት አይኖርም።[52] እንዲህ ያለው ጉዳይ ሲያጋጥም ሌላው መጤን ያለበት ነጥብ የይርጋው መጀመሪያ መቼ ነው የሚለው ጥያቄ ነው። አጠቃላይ በሆነው ደንብ መሠረት ማናቸውም ይርጋ መቆጠር የሚጀምረው አንድም ግዴታው መፈጸም ካለበት ወይም ግዴታው እንዲፈጸም የመጠየቅ መብት ሥራ ላይ ሊውል ከሚችልበት ቀን አንስቶ ነው።[53] በአንዳንድ ሁኔታዎች ግዴታው መፈጸም ያለበት ቀን የደረሰ ቢሆንም እንዲፈጸም ለመጠየቅ ያለው መብት ገና ወደፊት ያለ ቀን እስከሚደርስ ድረስ ሥራ ላይ ሊውል አይችልም። ይህ አንድም የፍርድ ወይንም ከዚህ በታች እንደሚታየው የሕግ ውጤት ሊሆን ይችላል። እንዲህ ባሉ አጋጣሚዎች የይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ግዴታው መፈጸም ካለበት ቀን አንስቶ ሳይሆን መብቱን ሥራ ላይ ለማዋል ከሚቻልበት ቀን አንስቶ ነው። እንግዲህ ይህንን አጠቃላይ ደንብ በመከተል ከይርጋው መቆጠር አጀማመር ጋር ተያይዞ ለተነሳው ጥያቄ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል።

ማናቸውም ግብር የመክፈል ግዴታ መፈጸም ያለበት በያንዳንዱ የግብር ዘመን መጨረሻ ሲሆን ይህም ዘመን እንደ ኢትዮጵያ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ያለው ጊዜ ነው።[54] ይሁን እንጂ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለው ግብር ከፋይ ያለበትን የግብር ዕዳ ወስኖ የመጠየቅ መብት ወዲያውኑ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል አይደለም። ይህ የሆነበት ምክንያት ግብር ከፋዮች ያለባቸውን ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር

የመክፈል ግዴታዎች በምን ያህል ጊዜ ውስጥ መፈጸም እንደሚኖርባቸው የሚደነግጉ ልዩ ድንጋጌዎች ስላሉ ነው።

የነዚህ ግዴታዎች አለመከበር የግብሩ አንድ አካል ሆነው ሊሰበሰቡ የሚችሉ መቀጫዎችን ያስከትላል፣ ስለዚህ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ግዴታዎቹ ስለመጣሳቸው ጉዳይ እርግጠኛ ለመሆን በሕግ የተደነገገው ወቅት ማለፍ አለማለፉን መከታተል አለበት። እንግዲህ መ/ቤቱ ያለውን የግብር ከፋዮችን የግብር ፋይ ወስኖ የመጠየቅ መብት ሊመሠረት የሚችለው ለእነዚህ ግዴታዎች መፈጸሚያ ተብለው በሕግ ከተደነገጉት መጨረሻ አንስቶ ስለሆነ የ10 ዓመት ይርጋው ከዚሁ ቀን አንስቶ መቆጠር ይጀምራል። ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የመቅረብና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች እንደነገሩ ሁኔታ፣ በአራ ወራት፣ በሁለት ወራትና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲፈጸሙ ሕጉ ይደነግጋል። ሁሉም ሁኔታ በሕግ የተደነገገው ወቅት መቆጠር የሚጀምረው ግብሩ ከሚመለከተው የግብር ዘመን መጨረሻ አንስቶ ነው።[55]

ለግዴታዎቹ መፈጸሚያ ተብለው በሕግ የተደነገጉት ወቅቶች ግብር ከፋዮች ከተመደቡባቸው ደረጃዎች ማለትም ሀ, ለ እና ሐ ጋር የተሳሰሩ ናቸው።[56] በዚህም የተነሳ እያንዳንዱን ግብር ከፋይ በተመለከተ ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ከመቼ አንስቶ ነው? የሚለው ጥያቄ መወሰን የሚገባው ግብር ከፋዩ የተመደበበትን ደረጃ መሠረት በማድረግ ነው። ይህን ጉዳይ የ1968 የግብር ዘመንን እንደምሳሌ በመውሰድ በይበልጥ ለማብራራት ይቻላል።

ከሐምሌ 1/1967 እስከ ሰኔ 30/1968 ያለው ጊዜ የተባለው የግብር ዘመን ነው። ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች መፈጸሚያ ተብለው በሕግ የተደነገጉት ወቅቶች መቆጠር የሚጀምሩት ከሐምሌ 1/1968 አንስቶ ነው። ግብር የመክፈል ግዴታው የበሰለው ሰኔ 30/1968 ስለሆነ በደረጃ ሀ, ለ እና ሐ ለተመደቡት ግብር ከፋዮች አግባብ የሆኑት በሕግ የተደነገጉ ወቅቶች የሚያከትሙት እንደቅደም ተከተሉ ጥቅምት 30/1969፣ ነሐሴ 30/1968 እና ሐምሌ 30/1968 ይሆናል። ይኸውም የይርጋን አቆጣጠር ስለሚመለከቱ ደንቦች በሚገልጸው ቁጥር ሥር አግባብ በሆነው ድንጋጌ መሠረት ነው።[57] (የግርጌ ማስታወሻ

ቁጥር 55ትን ይመለከቷል)። የያንዳንዱን በሕግ የተደነገገ ወቅት ማከተሚያ ተከትሎ ወዲያውኑ የሚመጣው ቀን እንግዲህ የ10 ዓመቱ ይርጋ መቆጠር የሚጀምርበት ይሆናል። ይርጋው የሚሞላበት የመጨረሻ ቀንም በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1848 በተገለጹት ደንቦች መሠረት ይወሰናል።[58]

2. <u>አንድ ግብር ከፋይ አግባብ በሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት ውስጥ እንድን የግብር ዘመን የሚመለከተውን ገቢውን ሁሉ ገልጾ በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር በሙሉ የከፈለበት ሁኔታ</u>፡

አሁን ለማየት በሚሞከረው ሁኔታ የሚነሳው የይርጋ ጭብጥ የሚወሰንበት መንገድ እምብዛም ውስብስብ አይደለም። የገቢው ግብር አዋጅ አንቀጽ 41 ልዩ ድንጋጌ ስለሆነ በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 ላይ የበላይነት ይኖረዋል። በመሆኑም የኋለኛውን ቁጥር እዚህ ላይ ማምጣት አስፈላጊ ሆኖ አይገኝም። በአንቀጽ 41 ድንጋጌ መሠረት የግብር ዘመኑን በሚመለከት የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለው የግብር ከፋዩን የግብር ዕዳ የመወሰን መብት ግብር ከፋዩ የገቢ መግለጫውን ካቀረበበት ቀን ከ5 ዓመት በኋላ ቀሪ ይሆናል። ይህ የ5ዓመት የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ግብር ከፋዩ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የገቢ መግለጫውን ካቀረበበት ከማግስቱም ቀን ሊሆን እንደሚችልና የግድ ለግዴታዎች መፈጸሚያ ተብለው በሕግ የተደነገጉት ወቅቶች ከሚያከትሙበት ቀን ማግሥት መሆን እንደሌለበት ማስተዋል ያሻል።

የ5 ዓመቱ የጊዜ ገደብ ካለፈ መ/ቤቱ የተጠቀሰውን ዘመን ዓመታዊ ገቢ የሚመለከት የግብር ውሣኔ ማድረግ አይችልም። ይህ ብቻ አይደለም። ግብር ከፋዩ ዘመኑን የሚመለከተውን ዓመታዊ ገቢውን ሁሉ ገልጾ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ግብር በሙሉ በሕግ በተደነገገው አግባብ በሆነው ጊዜ ውስጥ የከፈለ በመሆኑ መ/ቤቱ የሚሰበስበው ምንም ተጨማሪ ግብር አይኖርም። እንደ እውነቱ ከሆነ አግባብ በሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት ውስጥ ዓመታዊ ገቢ ሁሉ በተገለጸበትና በዚሁ ላይ የሚፈለገው ግብር በሙሉ በተከፈለበት ሁኔታ መብቱ ሳይሠራበት የ5 ዓመቱ የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ መ/ቤቱ ስለሚኖረው ግብር የመሰብሰብ መብት መናገር ትርጉም የለሽ ይሆናል።

ግብር ከፋዩ በሕግ የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሠነዶች የመያዝ ግዴታ ያለበት ሆኖ ግዴታውን ሳይፈጽም የቀረበት ሁኔታ እንዴት ይታያል?[59] ግብር የመወሰን መብት እንዲሠራበት ተብሎ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ካለፈ በኋላ መ/ቤቱ ላይ የተጠቀሰው ግዴታ በመጣሱ የሚጣለው መቀጫ ሊሰበሰብ ይችላልን? ይህ የሚያጋጥመው እጅግ አልፎ አልፎ ቢሆንም ጉዳዩ የሚያስገርም ይሆናል። የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ መቻል አለበት የሚል አቋም አለው። በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የተከፈለው ግብር መቀጫው የሚሠላበት መሠረት ይሆናል። መቀጫውን ለማስከፈል ክስ የማቅረብ መብቱ በአጠቃላይ ይርጋ ይገዛል።

3. <u>አንድ ግብር ከፋይ አግባብ በሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት አንድን የግብር ዘመን የሚመለከተው ዓመታዊ ገቢውን ሁሉ ገልጾ፣ ሆኖም በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር ሳይከፍል የቀረበት ሁኔታ፣</u>

በዚህ ሁኔታ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር መክፈል ወይም አለመክፈል የአንቀጽ 41ድን አፈጻጸም የሚነካ ነውን? የሚለው ጥያቄ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል። አውንታዊ የሆነውን ምላሽ የሚደግፍ አቋም ሊኖር እንደሚችል የሚገመት ስለሆነ ያለምንም ማምታታት የጭብጡን መፍትሄ መሻት ግድ ይሆናል። በዚህም ረገድ አውንታዊ የሆነውን ምላሽ የሚደግፉት ክርክሮች በቅድሚያ ቀርበው የዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ በጉዳዩ ላይ ያለውን አቋም የሚያሳዩት ክርክሮች ይከተላሉ።

ዓመታዊ የገቢ መግለጫ በመቅረብ ብቻ ግብር የመወሰን መብትን የሚመለከተው የ5 ዓመት የጊዜ ገደብ መቆጠር አይኖርበትም፣ የሚለው መነሻ መሠረቱ የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 46 ነው። ይህም ዓመታዊ ገቢው ሲገለጽ በዚሁ ላይ የሚፈለገው ግብር ወዲያውኑ መከፈል እንዳለበት ይናገራል። እንግዲህ አንቀጽ 46 በዚህ እረገድ ያሰፈረው ድንጋጌ ግልጽ ስለሆነ አንቀጽ 41 ተፈጻሚ መሆን ያለበት ሁለቱም ዓመታዊ ገቢን የመግለጽና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች ተሟልተው በተገኙበት ሁኔታ ብቻ ነው፣ የሚል መነሻ ሊቀርብ ይችላል። የዚህንም አስተሳሰብ ትክክለኛነት አጉልቶ ለማሳየት አንቀጽ 41 የታቀደው ለግብር ከፋዮች ጥቅም የሚሆን መብት ለመፍጠር እንደመሆኑ ግብር ከፋዮች ግዴታዎቻቸውን ሁሉ ባሟሉበት ሁኔታ

ሊጠቀሙበት አይችሉም፣ የሚል ተጨማሪ ክርክር ሊሰነዘር ይችላል። ከፍ ብሎ የቀረቡት ክርክሮች አሳማኝ መስለው ይታዩ ይሆናል። ይሁንና በሕግ መነጽር ሲመለከቷቸው የተዛቡ ናቸው።

በመጀመሪያ አንቀጽ 46 በሚገኝበት ክፍልና አንቀጽ 41 በሚገኝበት ክፍል መካከል ያለው የአላማ ልዩነት ከላይ የተገለጸውን አቋም የሚደግፍ አይደለም። አንቀጽ 46 የሚገኝበት ክፍል የታቀደው ግብር የመክፈል ግዴታን አፈጻጸም ለመወሰን ሲሆን ተደራሲውም ግብር ከፋዩ ነው።[60] በተቃራኒው አንቀጽ 41 የሚገኝበት ክፍል የታቀደው የግብር አወሳሰን ሥልጣንን አጠቃቀም ለመቆጣጠር ሲሆን የሚናገረውም ከግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ አንፃር ነው።[61] እቅጩን ለመናገር የአንቀጽ 41 ድንጋጌ በግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ግብር የመወሰን ሥልጣን ላይ የተደረገ ገደብ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ በአንቀጽ 41 ድንጋጌ ውስጥ ግብር የመክፈል ግዴታው መካተት በሰፊው ተቀባይነት ካላቸው የሕግ አተረጓጎም ደንቦች ውጭ መሥራት ይሆናል። የአንቀጹ ቋንቋ ግልጽና ምንም ዓይነት የአሻሚነት ምልክቶች የማይታዩበት ነው። ትርጉም በሚሰጥ መልክ ተፈጻሚ ሊሆን የሚችልባቸውም ሁኔታዎች ስላሉ ድንጋጌው ፍችህ አልባ ነው ሊባል አይቻልም። እንግዲህ አንድ ሰው በአንቀጽ 41 ውስጥ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ እንዲከተት የሚያደርገው የሕግ አውጭውን ተግባር ነጥቆ ወስዷል የመባል ስጋት እንዳለበት ይሆናል።

የሕግ ድንጋጌዎች እስከተቻለ ድረስ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ አድሎአዊ በሆነ አኳኋን መተርጎም አለባቸው፣ የሚል አጠቃላይ ደንብ መሆኑ ይታወቃል። ይህ የአተረጓጎም ደንብ ግን ቋንቋቸውና ዓላማቸው የጠራና የማያሻማ በሆኑ ድንጋጌዎች ውስጥ በዘፈቀደ ባይተዋር የሆኑ የማቋቋሚያ ሁኔታዎችን በማከተት የሚፈጸመውን ስሕተት አግባብ እንደሆነ አድርጎ ለማሳየት ያገለግላል ብሎ መቀበል አይቻልም። እንግዲህ ያለው አድራጎት ከላይ የተጠቀሰውን ደንብ አግባብ ባልሆነ አኳኋን መጠቀም ይሆናል።

በሦስተኛ ደረጃ በመሠረቱ የግብር ድንጋጌዎች በትክክል የታቀደላቸውን የአፈጻጸም ወሰንና የሚኖራቸውን ተፈጻሚነት ለማረጋገጥ አግባብ በሆኑና በሕሊና ርትዕ

ሆኖ በሚታይ ትርጉም ላይ መመርኮዝ ያስፈልጋል። ከአንቀጽ 41 ቋንቋ ለመረዳት እንደሚቻለው የሕግ አውጭው ዓላማ ማናቸውም ሌላ ሳይሆን በተገለጸው ገቢ ላይ በሆነ ያህል ጊዜ ውስጥ ግብር መወሰን እንዳለበት መደንገግ ነው። ለዚህም ድንጋጌ እንድ የተወሰነ የጊዜ ገደብ ቀርጦ የተባለው ጊዜ መቆጠር የሚጀምርበት ቀን ዓመታዊ የገቢ መግለጫው ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቀረበበትን ቀን እንዲሆን አድርጓል። በመሆኑም በድንጋጌው ውስጥ ዓመታዊ መግለጫ የተጠቀሰው በደርጋ አግባብ ማለትም የጊዜ ገደቡ መቆጠር የሚጀምርበትን ቀን ለማመልከት ብቻ መሆኑን መረዳት ይገባል።

አንቀጽ 41 የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ በሚቀርበው ዓመታዊ የገቢ መግለጫ አማካይነት ስለግብር ከፋዩ ገቢ መነሻ መረጃዎች ካገኘ በኋላ የግብር ልኩን በመወሰን ረገድ እንዲተጋ የሚያደርግ ዓላማ ያለው ድንጋጌ ነው። የጊዜ ገደብ ድንጋጌ እንደመሆኑም የአንቀጹ ዋና ጊዜው ሲያከትም[62] የባለሥልጣን መ/ቤቱን ግብር የመወሰን መብት ቀሪ ማድረግ እንጂ የግብር ከፋዮችን ልክ (ግዴታ) ማስቀረት አይደለም። የአንቀጽ 41 ዓላማም ለግብር ከፋዮች ጥቅም የሚሆን መፍጠር አይደለም። ይህ ነው ብሎ ማሰብ እንግዲህ የጊዜ ገደብ ያለውን ሚናና ዓላማ በቅጡ አለመገንዘብን ያሳያል።

በአራተኛ ደረጃ በአንቀጽ 41 ድንጋጌና በአዋጅ ቁጥር 77/1968 (እንደተሻሻለው) ውስጥ በሚገኘው አቻው ማለትም አንቀጽ 2 መካከል ንጽጽር ማድረግ ለጊዜ ገደቡ አፈጻጸም ወሳኝ የሆነው ምንድነው? በሚለው ጥያቄ ላይ ሕግ አውጭው ያለውን የዓላማ አንድነት ያሳያል።[63] አንቀጽ 26 ከእርሻ ሥራ የተገኘ ዓመታዊ ገቢ ሲገለጽ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለውን ግብር የመወሰን መብት አስመልክቶ ከላይ ከተጠቀሰው ጋር አንድ ዓይነት የሆነ የጊዜ ገደብ ይደነግጋል። ይህንንም ሲያደርግ ለጊዜ ገደቡ አፈጻጸም በተገለጸው ገቢ ላይ ግብር የመክፈል ግዴታ ቅድመ ሁኔታ መሆኑን ጨርሶ አልጠቀሰም። እንዲያው የሚገልጸው የጊዜ ገደቡ መቆጠር የሚጀምረው ዓመታዊ የገቢ መግለጫው ከቀረበበት ቀን አንስቶ መሆኑን ብቻ ነው። እንግዲህ ከፍ ብሎ ትችት በቀረበበት ድንጋጌ ውስጥ ካለው አቀራረብ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ይህ አቀራረብ ተቃራኒውን አመለካከት ሳይሆን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ የያዘውን አቋም የሚደግፍ ሆኖ ይገኛል። አግረመንገዱን የግብር ከፋይ ለጊዜ ገደቡ መቆጠር ቅድመ ሁኔታ ሆኖ በግልጽ የተጠቀሰባቸውን የትራንዛክሽን ታክስ አዋጅ ቁጥር 205/1955 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 15 ሐ እና አንቀጽ 21 ሐን ይመለከቷል።[64]

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ታኅሣሥ 16, 1986 ዓ.ም

በዚህ ረገድ መነሳት ያለበት ሁሉ እንደተባለ ይገመታል። ሆኖም በአንቀጽ 46 ዓመታዊ ገቢን የመግለጽና በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታዎች በአንድ ጊዜ ይፈጸሙ በማለት የተደነገገበት ምክንያት ምን ይሆን? የሚለውን ጥያቄ ማጤን ተገቢ ይሆናል። ይህም የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በትኩረት ላይ ካለው አቋም የተለየ አመለካከት ያላቸውን ሰዎች ሐሳብ እንደሚያረጋጋ ተስፋ ይደረጋል። ተቃዋሚ የግዴታዎች አለመከበር ከሚያስከትለው መቀጫ አንፃር መታየት ይኖርበታል። ምንም እንኳን በአንቀጽ 46 የተነገረው ያለ ቢሆንም ሕጉ ከሁለቱ ግዴታዎች እያንዳንዱን መጣስ የሚያስከትለውን እራሱን የቻለ መቀጫ ደንግጓል። በሕግ በተደነገገው ወቅት ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብ ግዴታ አለማክበር በአዋጁ አንቀጽ 66 የተመለከተውን መቀጫ ያስከትላል።[65] በተገለጸው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር በሕግ በተደነገገው ወቅት የመክፈል ግዴታን መጣስ ደግሞ በአዋጁ አንቀጽ 67 የተደነገገውን መቀጫ ያስከትላል[66] ሁለቱ ግዴታዎች በአንድ ጊዜ ይፈጸሙ በማለት ያሰፈረውን ያፋልሳል። አለማክበር ግን የሚያስከትለው መቀጫ በሕጉ አልተደነገገም። ግልጽ በሆነ አነጋገር አንድ ግብር ከፋይ ዓመታዊ የገቢ መግለጫ የማቅረብ ግዴታውንና በዚሁ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር የመክፈል ግዴታውን በአንድ ጊዜ አልፈጸመም በሚል ብቻ የሚጣልበት መቀጫ የለም። በመሆኑም ዓመታዊ ገቢውን በሕግ በተደነገገው ወቅት ውስጥ የገለጸ ሆኖም በተገለጸው ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር በወቅቱ ያልከፈለ ግብር ከፋይ መቀጫ የመክፈል ኃላፊነት የሚኖርበት በአንቀጽ 67 መሠረት ብቻ እንጂ በአንቀጽ 66 ጭምር አይደለም።

ይህ ከሆነ እንግዲህ በመተቸት ላይ ያለው የአንቀጽ 46 ኃይለቃል የታቀደው ግብር ከፋዮች ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ግዴታቸውን ለመወጣት ወደ ግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ዘንድ በሚመጡበት ጊዜ ሁሉ የገለጹትን ገቢ መሠረት በማድረግ ተሰልቶ የሚፈለግባቸውን ግብር ለመክፈል እንዲችሉ በቂ ገንዘብ ይዘው መቅረብ ያለባቸው መሆኑን ለማስታወስ ነው። የዚህም ዓላማ የግብር አሰባሰብ ተግባርን ቀና አመቺ ማድረግ ነው።

የታክስ ይርጋ

ለማጠቃለል አንድ ግብር ከፋይ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ በሕግ በተደነገገው ወቅት ዓመታዊ ገቢውን በገለጸበት ሁኔታ፣ ባለሥልጣኑ አግባብ በሆነው ጊዜ ውስጥ ሳይሠራበት ከቀረ ግብር ከፋዩ የገቢውን መግለጫ ካቀረበበት ከ5ዓመት በኋላ የተባለውን ዘመን በሚመለከት ግብር የመወሰን መብቱ ቀሪ ይሆናል። በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር አግባብ በሆነው ጊዜ ውስጥ አለመክፈል የሚያስከትለው በአዋጁ አንቀጽ 67 የተደነገገውን መቀጫ ነው። በማናቸውም መንገድ በአንቀጽ 41 የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ተፈጻሚ እንዳይሆን የማድረግ ውጤትን የሚያስከትል ሕጋዊ ምክንያት አይሆንም።

ባለሥልጣን መ/ቤቱ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገውን ግብር ለመሰብሰብ ያለው መብት ሊፋታዳይ ነው። በመመርመር ላይ ባለው ሁኔታ፣ ግብር ከፋዩ የግብር ዘመኑን በተመለከተ የከፈለው ምንም ግብር የለም። እንዲሁ እንደመሆኑ የባለሥልጣን መ/ቤቱ በተገለጸው ዓመታዊ ገቢ ላይ የሚፈለገው ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት የሚገዛው አጠቃላይ በሆነው የ10 ዓመት ይርጋ ነው። ዘመኑን በሚመለከት መ/ቤቱ ያለው ግብር የመወሰን መብት የ5ዓመት የጊዜ ገደቡ በማለፉ የተነሳ ቀሪ ከሆነ በኋላ እንኳ አጠቃላይ የሆነው የ10 ዓመት ይርጋ እስካላለፈ ድረስ ግብር የመሰብሰብ መብቱ ሊሠራበት እንደሚችል ማብራሪያ የሚሻ አይደም።

4. <u>አንድ ግብርከፋይ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ በሕግ የተደነገገው ወቅት ካለፈ በኋላ ዓመታዊ ገቢውን በሙሉ ገልጾ ሆኖም በገቢው ላይ የሚፈለገውን ግብር ጭራሽ ሳይከፍል የቀረበት ሁኔታ</u>፣

የግብር ከፋዩ እንዲሁ ያለው አድራጎት ቀጥሎ የተገለፁትን ሕጋዊ ውጤቶች ያስከትላል።

1. በመጀመሪያ መሥያ ቤቱ ያለውን ግብር የመወሰንና ክፍያውን የመጠየቅ መብቶች እስመልከቶ መቆጠር የጀመረውን የአሥር ዓመት ይርጋ ያቋርጣል።

2. የመሥሪያ ቤቱን ግብር የመወሰን መብት በተመለከተ የአምስት-ዓመቱ የጊዜ ገደብ መቆጠር እንዲጀምር ያደርጋል።

3. የመሥሪያ ቤቱን ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት በተመለከተ ደግሞ የአሥር ዓመቱ ይርጋ መቆጠር እንዲጀምር ያደርጋል።

ግብር ከፋዩ ዓመታዊ የገቢ መግለጫውን ሲያቀርብ ግብር የመክፈል ግዴታ ያለበት መሆኑን ማመኑ ነው። እንዲህ ያለው በጽሁፍ የተደረገ እምነት የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ያለውን ግብር የመወሰንና የመሰብሰብ መብቶችን በሚመለከት አግባብ የሆነው ሕግ የደነገገው ወቅት ካለፈበት ጊዜ አንስቶ መቆጠር የጀመረውን አጠቃላይ ይርጋ እንዲቋረጥ ያደርጋል።

ዓመታዊ ገቢ የሚገለጸው ለዚሁ ጉዳይ የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ባዘጋጀው ቅጽ ላይ እንደመሆኑ ቅጹን መሙላትና መፈረም ግብር የመክፈል ግዴታን በጽሁፍ መቀበልን ያሳያል።[67] በዚህም የተነሳ መግለጫው ከቀረበበት ቀን አስቀድሞ ያለፈው ጊዜ ሁሉ መታሰቡ ቀሪ ሆኖ አዲስ የአሥር ዓመት ይርጋ መቆጠር ይጀምራል።[68] ይርጋ ግን የሚቆጠረው ግብር የመሰብሰብ መብትን በተመለከተ ብቻ ነው። ምክንያቱም የገቢ መግለጫው መቅረብ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 41 የተመለከተ ድንጋጌ ተፈጻሚ እንዲሆን ስለሚያደርግ ነው።

የአምስት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ተፈጻሚነት የሚኖረው አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ዓመታዊ የገቢ መግለጫ አግባብ በሆነው ወቅት በቀረበበት ሁኔታ ብቻ መወሰን አለበት የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። እንዲህ ያለው አቋም ትክክለኛ ያለመሆኑን ለማሳየት ሲባል ቀደም ብሎ የአንቀጽ 41ን ዓላማ በሚመለከት የተገለጸውን እዚህ ላይ መልሶ መድገም ፋይዳ አይኖረውም። ስለዚህ በድንጋጌው ውስጥ የዚህን ሁኔታ አስፈላጊነት በግልጽም ሆነ በውስጠታዊነት የሚጠቁም አንዳች አነጋገር አለመኖሩን አጠናክሮ ማስገንዘብ ብቻ በቂ ይሆናል። አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ሕጉ በደነገገው ወቅት ውስጥ አለመቅረብ ከወቅቱ ውጭ ደግሞ ከመቅረቡ ጋር ሊቀርብ የሚችል ሲሆን በሁለቱም ሁኔታዎች አድራጎቱ አንቀጽ 41 ያለውን አፈጻጸም የሚነካ አይደለም። እንደመንገዱን ዓመታዊ የገቢ መግለጫ በሕግ በተደነገገው ወቅት ውስጥ የማቅረብ ግዴታን አለመፈጸም የሚያስከትለው ሌላው ሕጋዊ ውጤት ግብር በግምት እንዲወሰን ማድረግ እንደሆነ ይገነዘበዋል።[69]

5. <u>አንድ ግብር ከፋይ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ በሕግ የተደነገገው አግባብ የሆነው ወቅት ካለፈ በኋላ ዓመታዊ ገቢውን ሁሉ ገልጾ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ሙሉ ግብር የከፈለበት ሁኔታ</u>

ከፍ ብሎ የቀረቡት የአፈጻጸም ሐሳቦች በመብራራታቸው የተነሣ ይህንን ሁኔታ በሚመለከት የሚደረገውን ትንታኔ ለመረዳት ያን ያህል አያዳግትም። ግብር ከፋዩ ዓመታዊ የገቢ መግለጫውን አቅርቦ በዚሁ ላይ የሚፈለገውን ገቢ ሲከፍል ለግዴታዎቹ መፈጸሚያ በሕግ የተደነገገው አግባብ የሆነው ወቅት በማለፉ ምክንያት የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ያለውን ግብሩን የመወሰንና እንዲከፈል የመጠየቅ መብቶች እስመልከቱ መቆጠር የጀመረው የአሥር ዓመት ይርጋ ይቋረጣል። በምትኩ በአዋጅ

በአንቀጽ 41 ያለው የጊዜ ገደብ መቆጠር ይጀምራል። የሚያስከትላቸውን ውጤቶች ከፍ ብሎ በተራ ቁጥር 2 በቀረበው የአፈጻጸም ሃሳብ የተገለጸውን ነው። ይሁንና ይህ ሁኔታ የመቀጫ ጥያቄ የሚያስነሣ ሊሆን በተራ ቁጥር 2 የተብራራው ሁኔታ ግን የመቀጫ ጥያቄን የማያስነሳ መሆኑን ማስተዋል ይገባል።

6. <u>የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ላንድ ግብር ከፋይ እንዲደርሰው የተደረገበት ሁኔታ</u>

አጠቃላይ በሆነ አነጋገር በሕጉ አግባብ ለአንድ ግብር ከፋይ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ወጪ ሆኖ እንዲደርሰው መደረጉ ግብር የመወሰን መብት እንደተሟላበት ያመለክታል። በመሆኑም ስለ ይርጋ መናገር የሚቻለው በውሳኔው መሠረት ግብር እንዲከፈል ከመጠየቅ መብት በተያያዘ ነው።

ከይርጋ አኳያ አንድን የግብር ዘመን የሚመለከት ዋጋ ያለው የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው መደረግ ያለበት፦

ሀ/ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ጨርሶ ያልቀረበ ሲሆን በ10 ዓመት ውስጥ

ለ/ ዓመታዊ የገቢ መግለጫ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ የቀረበ ሲሆን ደግሞ በ5 ዓመት ጊዜ ውስጥ ነው።

ይህ ዓይነቱ ዋጋ ያለው የመጀመሪያ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው ሲደረግ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱን ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት

አስመልክቶ መቆጠር የጀመረው ማንኛውም የጊዜ ገደብ ይቋረጣል። ይህም የሚሆነው ከዚህ በታች የተገለፁትን ሕጋዊ ውጤቶች በማስከተሉ ነው።

አንድ ግብር ከፋይ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ውሣኔ እንደደረሰው ቀጥሎ ከተመለከቱት ነገሮች አንደኛውን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ እንዲፈጽም ሕጉ ይፈልግበታል።

1. ከግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጋር ተሳስቦ የሚፈለግበት ግብር ካለ እንዲከፍል /የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 46 ይመለከቷል/

2. የግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሲዮን ይግባኝ በማቅረብ መብቱ እንዲጠቀም /የአዋጅ ቁጥር 173/53 እንደተሻሻለው አንቀጽ 54 ይመለከቷል/

ግብር ከፋዩ ከላይ ከተጠቀሱት አማራጮች አንዱን እንኳ ሳይፈጽም የቀረ እንደሆነ ይርጋው የተቋረጠበት ምክንያት የሚፀናው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያው በአግባቡ ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው ከተደረገበት ቀን አንስቶ አንድ ወር ብቻ ነው። ከዚያ በኋላ የግብር ውሣኔ ማስታወቂያው ወዲያውኑ ተፈፃሚ እንዲሆን ሕጉ ስለሚደነግግ ልክ በፍ/ቤት እንደተሠጠ የፍርድ ውሳኔ ሆኖ ይታያል።[70] ሕጉ በግብር ውሣኔ ማስታወቂያው ላይ የተገለፀውን የግብር ዕዳ የመጨረሻና ትክክለኛ እንደሆነ አድርጎ ይቆጥረዋል። እንዲህም በመሆኑ ለግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ጥቅም የሚሆን የማስፈፀም ግዴታ ይፈጥራል።[71]

የግብር ውሣኔን ለማስፈፀም የመጀመሪያውን ማመልከቻ የማቅረብ መብት ልክ በፍ/ቤት እንደተሰጠ የፍርድ ውሣኔ በአጠቃላይ የአሥር ዓመት ይርጋ ውስጥ ሥራ ላይ መዋል ይኖርበታል። ይርጋው መቆጠር የሚጀምረውም ግብር ከፋዩ ከግብር ባለሥልጣን

መ/ቤቱ ጋር ለመተሳሰብ ወይም በአግራው ይግባኝ የማቅረብ መብቱን ለመጠቀም የተሰጠው የአንድ ወር ጊዜ የተፈፀመበት ቀን አንስቶ ነው። መ/ቤቱ በተባለው የአሥር ዓመት ይርጋ ውስጥ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያውን ለማስፈፀም ለፍ/ቤት የአፈፃፀም ማመልከቻ ካላቀረበ ግብሩ እንዲከፈል የመጠየቅ መብቱ ቀሪ ይሆናል።

ግብር ከፋዩ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ባሳለፈው የግብር ውሣኔ ላይ ለግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ይግባኙን አቅርቦ ክርክሩ በመካሄድ ላይ እያለ የመ/ቤቱ ክስ ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት ሥራ ላይ ሊውል እንደማይችል ግልጽ ነው። የኮሚሽኑ ውሣኔ ለባለሥልጣን መ/ቤቱ ከሆነ ከፍ ባለ የይግባኝ ደረጃ ሊለወጥ መቻሉ ሣይዘነጋ፣ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻና ተፈፃሚ ይሆናል።[72] በመሆኑም በግብር ይግባኝ ሰሚ ኮሚሽን ውሣኔ መሠረት በአፈፃፀም ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብት አሥር ዓመት ከማለፉ አስቀድሞ ለፍ/ቤት በሚቀርብ የአፈፃፀም ማመልከቻ ካልተሠራበት መብቱ ቀሪ ይሆናል።

የኮሚሽኑ ውሳኔ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱን የማይደግፍ ሲሆን ግብር እንዲከፈል የመጠየቅ መብቱ ታግዶ በሚቆይበት ልክ ይርጋው ይራዘማል። እዚህ ላይ መ/ቤቱ ኮሚሽኑ በሰጠው ውሳኔ ላይ ለመደበኛው የይግባኝ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ መብት አለው። ቀጥሎም የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኘው በጠቅላይ ፍ/ቤት ደረጃ ሊሆን ይችላል።[73] ለመ/ቤቱ የተወሰነ እንደሆነ እንዲሁ ያለውን ውሣኔ አፈፃፀም የሚገዛው ይርጋ የማናቸውንም ሌላ ፍርድ የሚገዛው ነው። በመሆኑም በአሥር ዓመቱ አጠቃላይ ይርጋ ውስጥ መ/ቤቱ ውሣኔውን ለማስፈፀም ምንም የአፈፃፀም ማመልከቻ ካላቀረበ ግብር እንዲከፈል መብቱን ያጣል።

7. <u>የግብር ባለሥልጣን መሥሪያ ቤት አሳልፎት የነበረውን የግብር ውሳኔ ለመለወጥና ለማሻሻል ያለው መብት</u>

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 41 እና 55 ድንጋጌዎች ያፈነገጠ እንደሆነ የሚገመተው የዚሁ ሕግ አንቀጽ 71 ሐ ግብር ከፋዮች በፈፀሙዋቸው የማጭበርበር ተግባሮች የተነሣ አንድን የግብር ዘመን በሚመለከት መክፈል በሚገባው የግብር ልክ ላይ የደረሰውን ጉድለት ለማስተካከል እንዲቻል ታቅዶ የተደነገገ ነው።[74] ግብር ከፋዮች፣

1. የገቢያቸውን ሙሉና ትክክለኛ መግለጫ ያላቀረቡ ወይም ለማቅረብ እምቢተኛ የሆኑ፣

2. የገቢያቸውን ልክ ምንጭና የሥራቸውን እንቅስቃሴ መጠን በሚመለከት መግለጫ ለማቅረብ እምቢተኛ የሆኑ ወይም እነዚሁኑ ጉዳዮች አስመልክቶ ሐሰተኛ የሆኑ መረጃዎች ያቀረቡ፣

3. በወንጀለኛ መቅጫ መሠረት የሚያስቀጣ ማናቸውንም ገብር ነክ ወንጀል የፈፀሙ ሆነው ሲገኙ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ቀደም ሲል አሳልፎ የነበረውን የግብር ውሳኔ የማሻሻል ወይም የመለወጥ መብት ተሠጥቶታል። እግረ መንገዱን አንቀጽ 70 ሐ 1 የአንቀጽ 41 ድንጋጌ የመጨረሻው ሐረግ ቃል ያስከተለው ውጤት ሆኖ እንደሚገመት ያስገነዝባል። የተጠቀሰው ሐረግ ቃል የአምስት ዓመቱ የጊዜ ገደብ ማለፍ ግብር ከፋዮችን በገቢ መግለጫቸው ባልገለፁት ገቢ ላይ ለሚፈለገው ግብር ከመጠየቅ እንደማያድናቸው ይገልፃል።[75]

እንቀጽ "70-ሐ-" ከዶርጋ አገኘር ሲታይ በድንጋጌው ውስጥ ያሉት ቁልፍ የሆኑ ቃላት "በማናቸውም ጊዜ" የሚሉት እንደሆኑ መረዳት አያስቸግርም። እነዚህ ቃላት የባለሥልጣን መ/ቤቱ ከፍ ብሎ የተጠቀሱት የማጭበርበር አድራጎቶች መፈፀማቸውን ከማወቁ ጋር ተያያኝተው ሲታዩ ምን ዓይነት አስተሳሰብ ያሳድራሉ። ወሳኙ ጥያቄ ይህ ሲሆን ጥያቄውን በሁለት መንገዶች ማየት ይቻላል።

በመጀመሪያ "በማናቸውም ጊዜ" የሚሉትን ቃላት ፍፃሜ በሌለው ጊዜ አግባብ መመልከት ይቻላል። በዚህ አመለካከት መሠረት የአለፉት ዓመታት ብዛት የቱን ያህል ቢሆንም መ/ቤቱ አንድን የግብር ዘመን በተመለከተ አንድ ግብር ከፋይ ከፍ ብሎ ከተጠቀሱት የማጭበርበር አድራጎቶች ማናቸውንም መፈፀሙን በደረሰበት ጊዜ ሁሉ የግብር ዘመኑን የሚመለከተውን የቀድሞ የግብር ውሳኔ አሻሽሎ ወይም ለውጦ ግብሩን እንደአዲስ መወሰን ይችላል። ይህ አስተሳሰብ የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያለውን አማልሮ የነበረውን የግብር ውሳኔ የማሻሻል ወይም የመለወጥ መብት ከዶርጋ ደንቦች አፈፃፀም ከምንም ገደብ ውጪ ነው ወደሚለው መደምደሚያ ያደርሳል።

እርግጥ በዚህ ሁኔታ መ/ቤቱ የማጭበርበር አድራጎት መፈጸሙን ካወቀበት ጊዜ አንስቶ ባለው የ10 ዓመት ጊዜ ውስጥ በተባለው መብት ሳይጠቀምበት በመቅረቱ መብቱ ቀሪ ሊሆን በሚችልበት አጋጣሚ ሊኖር እንደሚችል ይገመት ይሆናል። ይህ ግምት ግን እጅግ በጣም የራቀ ነው። ምክንያቱም መ/ቤቱ ይህን ያወቀበትን ትክክለኛ ቀን አስረድቶ በዶርጋ መከላከያ ለመጠቀም ግብር ከፋዩ መቻሉ የማይመስል ነገር ስለሆነ ነው።

በሁለተኛው መንገድ "ማናቸውም ጊዜ" የሚሉትን ቃላት በፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር 1845 በተመለከተው አጠቃላይ የዶርጋ ድንጋጌ አግባብ ማየት ይቻላል። በዚህ አመለካከት ላይ በመመሥረት የሚከተለው ሃሳብ ቀርቧል።

የግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱ አንድን የግብር ዘመን የግብር ውሣኔ በሚመለከት የተፈጸመውን የማጭበርበር አድራጎት ተከታትሎ ሊደርስበት (ሊያውቀው) የሚገባውና የግብር እዳውን እንደገና የመወሰን መብቱን ሊሠራበት የሚችለው በ10 ዓመት ውስጥ ሊሆን ጊዜው መቆጠር የሚጀምረው፦

1. አንቀጽ 41 ድንጋጌ መሠረት ግብር ከፋዩ በገለጸው ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር ትክክለኛ እንደሆነ ከሚቆጠርበት ቀን አንስቶ፣[76]

2. ለግብር ከፋዩ እንዲደርሰው የተደረገው የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ በአንቀጽ 55 መሠረት የመጨረሻና ትክክለኛው ሆኖ ከሚቆጠርበት ቀን አንስቶ ይሆናል፣[77]

ከፍ ብሎ ከተረቡት ሁለት አስተሳሰቦች የኋለኛው ተቀባይነት ሊኖረው ይገባል። ይህም የሚባልበት በሚከተሉት ምክንያቶች ነው።

1. አጠቃላይ በሆነ አነጋገር ቀደም ሲል የይርጋ ደንቦች ለምን መደንገግ እንዳስፈለጋቸው ሲወሳ የተገለጹት የቲዎሪና ሕግ ነክ ምክንያቶች ሁሉ ሁለተኛውን አስተሳሰብ የሚደግፉ ናቸው።

2. ይልቁንም የቀድሞውን የግብር ውሣኔ ማስታወቂያ ሽር ግብሩን እንደአዲስ የመወሰን መብት በግብር ባለሥልጣን መ/ቤቱና በግብር ከፋዩ መካከል የቆየ ግንኙነት እንዳለ ግምት የሚያሳድር ስለሆነም የተባለው መብት ለሁል ጊዜ ፋይዳውን እንደያዘ እንዲቆይ መፍቀድ ምክንያት የለሽ ይሆናል።

3. ሁለተኛው አማራጭ በአንድ የሒሣብ ዓመት በግብር ከፋዩ ላይ የሚጣለውን የግብር ዕዳ በቁጥር ተወስኖ የሚታወቅበትን ቀን ለመለየት የሚያስችል ትክክለኛና ትርጉም የሚኖረው የስሌት መንገድ የሚሰጥ ነው።

4. የቀረቡ የግብር ውሳኔ ማስታወቂያን በማሻሻል ወይም በመለወጥ ግብሩን እንዲያሻሽል የመወሰን መብት በገቢ ላይ ወንጀል ፈጻሚ የሆኑ ግብር ከፋዮችን እድሜ የመያዝ ግዴታን በሚያካትት ሁለተኛው አስተዳደር መ/ቤቱ ይህን ኃላፊነቱን ለመወጣት በትጋት እንዲተር ከማድረግ ጋር በተያያዘ የተቀናጀ ሆኖ ይገኛል። መ/ቤቱ በሥሩ ያለውን የኢንስፔክሽን ኃይል በብቃት እንዲያሰማራና ለተባለው ዓላማ አግባብ ካለው የመንግሥትና ሕዝባዊ ድርጅቶች በቀለጠፈ አኳኋን ዕርዳታና የሥራ ትብብር እንዲጠይቅ ተጽእኖ ያደርጋል።

የግብር ሕጎች የዶርጋ ጉዳዩን በቂ በሆነ መንገድ የሚደነግጉ ድንጋጌዎችን የያዙ እንዲሆኑ ማድረግ ግድ ነው። ይህን በሚመለከት መደረግ ስለሚገባቸው ነገሮች ኃሳቦች ማቅረብ ያን ያህል ከባድ ላይሆን ይችላል። ላሩ ግን በልምድ እንደታየው እንዲህ ያሉ የግብር ማሻሻያ ሃሣቦች ፈጥነው በተግባር ለመተርጎም አለመቻላቸው። ሆኖም እስከዚያው ድረስ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ እንደተነሱት ላሉ የሕግ ችግሮች አግባብ ባላቸው የፍትሐብሔር ሕግ ድንጋጌዎች እየታገዙ መፍትሄ መስጠት ግድ ይሆናል። ተደም ሲል በተገለጸው አኳኋን በፍትሐብሔር ሕግ መገልገል በሕግ ያልተከለከለ በመሆኑ በዚሁ ሕግ ባግባቡና ሳያወላውሉ መገልገልን የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ ያበረታታል።

ከፍ ብሎ ስለ ዶርጋ አፈጻጸም የቀረቡት ሃሣቦች በግብር ክሶች ላይ አሁን ካለው አመለካከት የተለዩ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲያውም አንዳንዶቹ ፍ/ቤቶች ግብር ነክ የዶርጋ

ጭብጦችን በመወሰን ረገድ ሊከተሉት ከቆዩት ሥር ነቀል በሆነ መንገድ ሊለዩ ይችላሉ። ይሁንና በግብር መስክ ይርጋን የሚገዙ ዝርዝር ደንቦች በሌሉበት ሁኔታ የቀረቡት ሃሳቦች ከማናቸውም ይልቅ በተግባር ሊገለጡ የሚችሉ እንደሆነ ይገመታል። በዚህም የዚህ ጽሁፍ አቅራቢ እርካታ ያገኛል።

## ማስታወሻዎችና ማጣቀሻዎች

1. የሁለቱ አንቀጾች እንደተራ ቁጥራቸው "በይርጋ ቀሪ የማይሆኑና" እና "በይርጋ ቀሪ የሚሆኑ" ተብለው ይተረጎማሉ።

2. Rudof Shom, The Institute of Roman Law (Oxford: Clarendon Press, 1901), ከገጽ 298-300.

3. ዝኒ ከማሁ

4. <u>International Encyclopaedia of Comparative Law</u> "Period of limitation" (Dordrechf, Boston, Lancaster: Tuebirgen and Martinus Nijahoff Publishers, 1986, Vo. XI, part II, Chapter 13, ገጽ 23.

5. በኮመን ሎው ሥርዓት ላቾስ በመባል የሚታወቀው መከላከያ ከሳሽ ክስ የማቅረብ መብቱን ሳይጠቀምበት መዘግየቱን ምክንያት በማድረግ የተጀመረ ክስ እንዳይቀጥል ተከሳሽ ሊያነሳው የሚችል መከላከያ ነው። የዘገየበት ጊዜ ከተከሳሽ ቸልተኝነት ወይም የትጋት ጉድለት መንጭቶ የተከሳሽን ጥቅም ይነካል። የሚያሰኝ መሆን ወይም ከሳሽ የመከሰስ መብቱን ፈቅዶ ትቷል ሊያሰኝ በሚችል መጠን የረዘመ መሆን ይኖርበታል። እዚህ ላይ "ይርጋ" ና "ላቾስ" አንድ አለመሆናቸው ያስተውሏል። የመጀመሪያው ክስ ለማቅረቢያ በህግ የተደነገገውን ጊዜ የሚያመለክት ሲሆን የኋለኛው በህግ ድንጋጌዎች ላይ ሳይመሠረት ክስን በማቅረብ ረገድ በሀሊና ግምት ከተገቢው በላይ መዘግየትን የሚያመለክት ነው።

6. International Encyclopoedia of Comparative Law, ገጽ 23

7. በፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ. 1165(2)፣ 1192፣ 1000፣ 1810፣ 1024፣ 2143 የወንጀለኛ መቅጫ ቁ. 226-231.

8. Philip S. James, Introduction to English Law (London: English Language Books Society and Butter Worth, 10th Edition, 1984 p. 301.

9. Rene David, Commertany on Contracts in Ethiopia, Translated by Michael Kindred (Addis Ababa, Haile Selassie I University, Faculty of Law. 1973), ገጽ 89.

10. Marcel Planiol. Treatise on the Civil Law, Transated by Louisiana State law Institute (Paris: Loulsiara State law Institute, 1959, ከገጽ 345-356.

11. Corpus Juris Secundum, Taxation (St. Pau, Minne Sota, West Publishing Co., 1954), Vol. 84, p. 1429.

12. ዝኒ ከማሁ ገጽ 1430.

13. እዚህ ሁኔታዎች ከግብር ጋር ምንም ግንኙነት የሌላቸው መሆኑን ያስተውሏል። እንደጠቆ ወደፊት ባለቤት እሌባ እንደሆኑ የተቀጠሩ ንብረቶችን በሚመለከት የባለሃብትነት መብቶችን ከማስተላለፍ ጋር የተያያዙ ናቸው።

14. Planiol, ከገጽ 378-380.

15. Corpus Juris Secundum, ገጽ 46.

16. የግብር ዕዳ መግርን በተመለከተ ምሳሌ ይሆን ዘንድ አዋጅ ቁጥር 173/1958 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 72/35 የአዋጅ ቁጥር 77/1968 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 45ን ይመለከቷል።

17. World Tax Series, <u>Taxation in Brazil</u> (Boston, Toronto; Little, Brown and Company Limited, 1957, ገጽ 262.

18. ዝኒ ከማሁ

19. ዝኒ ከማሁ ከገጽ 262-263.

20. <u>World Tax Series, Taxation in Italy</u> (Chicago: Common Clearing Houses Inc., 1964), ከገጽ 248-249.

21. Word Tax Series, <u>Taxation in Sweden</u> (Canda: Little Brown and Company Limited, 1959), ገጽ 592.

22. World Tax Series,, <u>Taxation in the Federal Repubic of Germany</u> (Chicago; Commerce Clearing House Limited, 1963), ከገጽ 686-688.

23. ዝኒ ከማሁ

24. አዋጅ ቁ. 145/1947, አንቀጽ 106 ማናቸውም ቀረጥ በሙሉ ሳይሆን በጎደል በተቀረጠ ወይም በስህተት በተመለሰ ጊዜ ቀረጡን በሙሉ ሳይከፍል የቀረ ወይም ቀረጡ በስህተት የተመለሰለት ሰው ቀረጡ ጎድሎ ከቀረበበት ወይም ከተመለሰለት ቀን አንስቶ እስከ አምስት ዓመት ድረስ ዲሬክተሩ በጠየቀው ጊዜ የጎደለውን ቀረጥ ወይም በስህተት የተመለሰለትን ቀረጥ ይከፍላል።

25. አዋጅ ቁ. 173/1953 አንቀጽ 4/ አንድ ግብር ከፋይ የገቢውን ማስታወቂያ ለአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን አቅርቦ የተባለው የገቢ ማስታወቂያ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ በአምስት (5) ዓመት ጊዜ ውስጥ ከተገለጸው ተከፋይ ግብር የተለየ የግብር ውሳኔና መደብ ማስታወቂያ ግብር ከፋዩ እንዲደርሰው ካልተደረገ በስተቀር ግብር እንዲከፈልበት የተገለጸው ገቢ በቂ ሆኖ ግብሩ የተወሰነውና የተመደበው በዚሁ ገቢ ላይ ብቻ ሆኖ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ በዚህ በአንቀጽ 41 ውስጥ የተሰጠ ውሳኔ በተባለው የገቢ ማስታወቂያ ውስጥ ካልተገለጹት ገቢዎች ግብር ከፋዩን የገቢ ግብር ከመክፈል ነፃ አያደርገውም

በዋናው አዋጅ አንቀጽ 41 የተመለከተው የሦስት ዓመት ጊዜ በአዋጅ ቁጥር 65/1968 ወደ አምስት ዓመት መሻሻሉን ይገነዘቧል።

26. የፍትሐ ብሄር ሕግ ከቁጥር 1845-1856

27. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1677። የዚህ አንቀጽ አፈጻጸም</u>

1. ግዴታዎች ከውል የተገኙ ባይሆኑም የዚህ አንቀጽ ደንቦች ይፈጸሙባቸዋል።
2. የአንዳንድ ግዴታዎችን ከበር አመጣጣቸውን ወይም አይነታቸውን በመመልከት ከዚህ ጸንብ የተለዩት ደንጋጌዎች የተጠበቁ ናቸው።

28. <u>የፍታብሔር ሕግ ቁ 1875። የድርጋ ጊዜ</u>

ሕግ በሌላ አኳኋን ካልወሰነ በቀር ውሉ እንዲፈጸም ወይም ካለመፈጸሙ የተነሣ ለሚደርስ ጉዳት ወይም ውሉ እንደፈርስ የመጠየቅ መብት በዐሥር ዓመት ድርጋ ይቀራል።

29. Rober Warden Lee, <u>The Elements of Roman Law</u> (London: Sweet and Maxwell, 1956), ገጽ 256.

30. ዝኒ ከማሁ።

31. Amos and Walton, <u>Introduction to French Law</u> (Oxford: Calredon Press, 1969), ገጽ 140.

32. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 70 (ሀ) በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱትን ማናቸውንም ውሳኔዎች የሚተላለፍ ወይም የሚጥስ ግብር ከፋይ በ1949 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል።

33. <u>የፍትሐብሔር ሕግ ቁ 2139። የወንጀል ፍርድ ቤት በፍትሐብሔር ስላለው ሥልጣን።</u>

በፍትሐብሔር በኩል ጥፋት ተደርጓል ብሎ ለመወሰን በወንጀል ፍርድ ተከሳሹ ነፃ መለቀቁ ወይም በወንጀል አያስከስሰውም ተብሎ መበየኑ ዳኞቹን አያግዳቸውም፡

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ 232። <u>በፍትሐ ብሔር በኩል የይርጋ ዘመን መጽናት የሚያስከትለው ውጤት</u>

ስለ ጥፋት ማካካሻ ካሳ አከፋፈል በፍትሐ ብሔር በኩል እንዲጸና የሚታሰበውን የይርጋ ዘመን ጊዜ ውሳኔ የሚመለከተው ነገር ከወንጀል ክስ ጋራ ቢቀርብም ባይቀርብም ይጸናል የሚያስኘበት ስርዓትና የጊዜው ውሳኔም ሆነ የይርጋው መፅናት በሚያስከትለው ውጤት በኩል ያለው የጉዳዩ አፈፃፀም የሚመራው በፍትሐብሔር ህግ ደንበኛ ድንጋጌዎች ውስጥ ነው።

በፍትሐ ብሔር በኩል ያለው ክስ በይርጋ ቀሪ ሳይሆን የወንጀሉ ክስ ማቅረቢያ ጊዜ በይርጋ ቀሪ ሆኖ እንደሆነ ይህ የፍትሐብሔር ጉዳይ በወንጀል ፍርድ ቤት ችሎት ቀርቦ ሊታይ የማይችል በመሆኑ የክፍሉ ባለሥልጣን በሆነው በፍትሐብሔር ፍርድ ቤቶች ችሎት ፊት ቀርቦ ሊታይ ይገባዋል።

34. <u>Corpus Juris Secundum</u>, ገጽ 32.

35. በዚህ ረገድ የሚከተሉትን ሁለት የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥሮች ያነጻጽሩአል። <u>1833። መቻቻያን የሚያስደርጉ ሁኔታዎች</u>።

ቀጥሎ ከተዘረዘረው በቀር የዕዳው ምክንያት ማናቸውም ዓይነት ቢሆን ማቻቻያ ይደረጋል።

(ለ) ለመንግሥትና ለመሥሪያ ቤቶች የሚከፈል ግብር ቢሆን፤ ቁ <u>3178 ስለ ማቻቻል</u>

ተዋዋይ ዕዳ ይቻቻላል ብሎ ያስተላለፈን መሥሪያ ቤት ለመጠየቅ የሚችለው ያቻቻሉኝ የሚለው ዕዳ የቀረጥ ዕዳን የሚመለከት ያልሆነ እንደሆነ ነው።

በአማርኛው የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር 1833 (ለ) እና ቁ 3178 መካከል በእንግሊዝኛው ቁጥር እንደሚታየው ያለ መቃረን አለመኖሩን ይገነዘቡአል። ሁለቱም ዕዳን የግብር ዕዳን ለማቻቻል መታወቂያ ማቅረብ አለመፈቀዱን ይገልጻሉ።

36. David, ገጽ 7.

37. George Krzeczunowicz, <u>Formation and Effects of Contracts in Ethiopian Law</u> (Addis Ababa: Faculty of Law, Addis Ababa University, 1983), p.v. (preface).

38. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1676 ውሎች የሚመሩባቸው ደንቦች</u>

1. ውሎች ዐይነታቸውም ምክንያታቸውም ማንኛውም ቢሆን በዚህ አንቀጽ በተጻፉት ጠቅላላ ደንቦች ይመራሉ።

2. እነዚህን ጠቅላላ ደንቦች የሚለውጡ ወይም የሚያሟሉ ስለ አንዳንድ ውሎች የተደነገጉ ልዩ የሆኑ ደንቦች በዚሁ ሕግ በ5ኛው መጽሐፍና በንግድ ሕግ ውስጥ ተመልክተዋል።

39. Krzeczunowicz, ገጽ 1.

40. ዝኒ ከማሁ

41. ዝኒ ከማሁ

42. David, ገጽ 89.

43. Robert Allen Sedler, Ethiopian Civil Procedure (Addis Ababa: Faculty of Law, HSIU in Association with Oxford University Press, 1968). p. 271.

44. David, ገጽ 89

45. የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1288። መሠረት።

1. የማይንቀሳቀስ ንብረት ባለእጅ (ባለይዞታ) የሆነ ሰው የዚሁ ንብረት ግብር ባለማቋረጥ 15 ዓመት በሙሉ ከከፈለ የዚሁ ሀብት ባለቤት ይሆናል።

ይህ ድንጋጌ የግል ባለርስትነት ቀሪ ባደረገው ሕግ ከ1967 ወዲህ ተፈጻሚነት እንዳይኖረው ሆኖአል።

<u>ቁ 1000 (2) ጥያቄውን ለማቅረብ የተወሰነ ጊዜ።</u>

1. ከሳሽ መብቱንና የውርሱ ንብረቶች በተከሳሹ መያዛቸውን ካወቀ ሦስት ዓመት ካለፈ በኋላ ስለ ወራሽነት ጥያቄ የሚያቀርበው ክስ ተቀባይነት ለማግኘት አይችልም።

2. እንደዚሁም ሟቹ ባለንብረት ወይም ከሳሹ በመብቱ ለመሥራት ከቻለበት ቀን አንሥቶ ዐሥራ አምስት ዓመት ካለፈ በኋላ ከዘር የወረደ ርስት ካልሆነ በቀር የተባለው የውርስ ጥያቄ ክስ በማናቸውም አስተያየት ቢሆን ተቀባይነት አያገኝም።

46. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው)። አንቀጽ 4 (ለ) በገጠር መሬት መጠቀሚያ ክፍያና የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር፥ አዋጅ ቁጥር 77/1968 ዓ.ም (እንደተሻሻለ) ሥር የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ከንግድ፥ የፐርፌሽን (ሙያ) ከማሊቃ ገብ ሥራ (ቮኬሽን) እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ፥ ሐ፥ መ፥ ሠ፥ እና ረ ከተመለከቱት ውጭ ከማናቸውም ሌላ የሥራ እንቅስቃሴ በሚገኝ ገቢ ላይ ከዚህ በታች ከአንቀጽ 12 እስከ 17 ቁጥር (ሠንጠረዥ ሐ) በተመለከተው መሠረት።

47. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው)

5ኛ/ ሠንጠረዥ "ሐ"

አንቀጽ 12 (ሀ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 4 በንዑስ አንቀጽ (ለ) ከተጠቀሱት የገቢ ምንጮች ላይ ግብር እየተወሰነና እየተመደበ በየዓመቱ ይከፈላል፡ ይሁን እንጂ የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን የተለየ የሂሣብ ዓመት እንዲሆን ካልፈቀደ በስተቀር ግብሩ የሚከፈለው ከኢትዮጵያ መንግሥት የበጀት ዓመት ጋር ተመሳሳይ ከሆነው ከኃላፊው የሂሣብ ዓመት ግብር ከሚከፈልበት ገቢ ላይ ነው።

48. የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ስለ ግብር ከፋዮች የሥራ እንቅስቃሴና ገቢ መረጃዎች የማግኘት መብቱን በሚገባ የሚጠቀምበት ቢሆን (አዋጅ ቁ 173/1953 እንደተሻሻለው አንቀጽ 23-27)፡ እንዲሁም ንግድን ወይም መድበልን ለማካሄድ የንግድ ፍቃድ ማውጣት አስፈላጊ ስለመሆኑ የተደነገጉት ድንጋጌዎች በሚገባ ሥራ ላይ የሚውሉ ቢሆን (የአዋጅ ቁ 294/1963 አንቀጽ 3(1) በአዋጅ ቁ 76/1968 አንቀጽ 11 እንደተሻሻለው) ይህ ሁኔታ የሚያጋጥመው እጅግ በጣም አልፎ አልፎ ነው።

49. የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1196። ሀብትነትን የሚያስቀር የይርጋ ዘመን።

ግዙፍነት ያለው ያንድ የሚንቀሳቀስ ንብረት ባለሀብት ሀብቱ የሚገኝበትን ቦታ ወይም ሀብቱ መሆኑን ባለማወቅ በዐሥር ዓመት ያልተገለገለበት እንደሆነ መብቱን ያጣ ሆኖ ይቀራል።

50. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1853። የመጋባት ወይም የቤተዘመድ ግንኙነት</u>

1. ፍርድ ቤቱ ይርጋን አለቀበለም ለማለት የሚቻለው ባለገንዘቡ የሚፈልገውን ያልጠየቀበት ምክንያት ባለዕዳውን የመፍራትና የማክበር ስሜት ኑሮት ለሱም የተቀራረበ ዝምድና ወይም ቃዝኝነት ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው።

2. እንዲሁ ቢሆንም ዕዳውን ለመክፈል ዋስ የሆኑት ሰዎች ከግዴታቸው ነፃ ይሆናሉ።

51. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ 1854። ክፉ ልቦና</u>። ይርጋ እንዳይቆጠርበት ክፉ ልቡናን መቃወሚያ አድርጎ ለመከራከር አይቻልም።

52. አንዳንድ ሰዎች በቀረበው ክርክር አጥፊ ግብር ከፋዮች ሊጠቀሙ ይችላሉ በሚል ሐሳብ ቅሬታ ይገባቸው ይሆናል። ይሁን እንጂ ትንታኔውን በሕጉ ዓይን ቢመዝኑት የተሻለ ይሆናል። እንደውነቱ ከሆነ ይበልጥ ከባድ እንደሆኑ የሚቆጠሩት የወንጀል ክሶች እንኳን፣ ቀደም ሲል እንደተገለጸው በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ። እንግዲ መንገዱን ከባድ ለሆነው የግብር ወንጀል የተደነገገው መደበኛ የይርጋ ዘመን 5 ዓመት ነው። (የወንጀለኛ መቅጫ ቁ 226 (ሠ) ን ከ 355 (1), 360 (1) እና 361 (1) እንዲሁም ከአዋጅ ቁ 214/1973 አንቀጽ 15 ጋር አጣምሮ ይመለከቷል።) በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ቁ 231 በተመለከተው ደንበኛ መሠረት ከባድ ለሆነ የግብር ወንጀል የተደነገገው ፍጹም የሆነ የይርጋ ዘመን አስር ዓመት ነው። ይርጋው መቆጠር የሚጀምረው ወንጀል ፈጻሚው የመጀመሪያ የወንጀል ድርጊቱን ከፈጸመበት ቀን አንስቶ ነው። (የወንጀለኛው መቅጫ ሕግ ቁ 228 (2) ይመለከቷል።)

53. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ ፩866። የይርጋው መነሻ ጊዜ።</u>

የይርጋ ቀን መቁጠር የሚጀምረው ግዴታውን ለመጠየቅ ተገቢ ከሆነው ወይም ውሉ የሚሰጠው መብት ከተሠራበት ቀን ጀምሮ ነው።

54. አዋጅ ቁ 162/1951 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 2 የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 ቀን ጀምሮ እስከሚቀጥለው ዓመት ሰኔ 30 ቀን ድረስ ላለው የአንድ ዓመት ጊዜ ይሆናል።

አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 35 (ሐ) በዚሁ አዋጅ በመንጠረዥ "ሐ" በተመለከተው መሠረት ግብር ከሚከፈልበት የገቢ ምንጭ ስለሚገኝ ገቢ በየዓመቱ ከዚሁ በታች እንደተመለከተው ማስታወቂያ ይቀርባል።

1. የገንዘብ ሚኒስትር በሚያወጣው ደንብ መሠረት ግብር ከፋይ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ እንዲኖር የተወሰነ እንደሆነና በየዓመቱ መጨረሻ ለአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን ከአስፈላጊው ዝርዝር መግለጫ ጋር ባላንስ ሺትና የትርፍና ኪሣራ ሂሳብ የሚያቀርብ ሲሆን፣ ግብሩን ከሚከፈልበት የሂሳብ ዓመት መጨረሻ አንስቶ እስከ አራት 4/ ወር ድረስ፣

2. የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው ደንብ መሠረት ከፋዩ ለአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን የየቀኑን ጠቅላላ ገቢና ወጪውን ተከፋፍሎ ወይም ሳይከፋፈል ወይም ደረጃ በደረጃ/በግሩፕ ለማቅረብ በሚችልበት አኳኋን ብቻ መዝገብና የሂሳብ መግለጫ እንዲኖር የተወሰነ እንደሆነ ግብሩ የሚከፈልበት የሂሳብ ዓመት መጨረሻ አንስቶ እስከ(፫) ወር ድረስ፣

3. ግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ወይም መግለጫ እንዲኖረው ካልተወሰነ ግብሩ ከሚከፈልበት የሂሳብ ዓመት መጨረሻ አንስቶ እስከ ሠላሳ(፴) ቀን ድረስ።

56. የግብር ከፋዮች አመዳደብና የሂሣብ መዛግብትና ደጋፊ ሠነዶች የመያዝ ግዴታ በተመለከተ የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁ 258/1955, ከአንቀጽ 25-95 ያሉትን ድንጋጌዎች ይመለከቷል።

57. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ ፩808። በወሮች የተወሰነ ጊዜ።</u>

1. ጊዜውን በወር ወይም በብዙ ወሮች የተወሰነ እንደሆነ ዕዳውን ለመክፈል የሚገባው ውሉ በተደረገበት ቀን በመጨረሻው ወር መጨረሻ ቀን ነው። 3 ጳጉሜ እንደ አሥራ ሦስተኛ ወር አይቆጠርም።

58. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ ፩838። የጊዜው አቆጣጠር።</u>

1. የይርጋ መጀመሪያ ቀን ከይርጋው ዘመን ሂሳብ ውስጥ ገብቶ አይታሰብም።
2. የይርጋው ቀን የሚቆጠረው ለይርጋው የተወሰነ መጨረሻ ቀን ካለፈ በኋላ ነው።
3. ምናልባት ይህ ቀን ገንዘቡ በሚከፈልበት ቦታ በሕግ የታወቀ የበዓል ቀን የሆነ እንደሆነ ይርጋው የሚቆጠረው ከበዓሉ ተከታይ በሆነው በዓል ባልሆነው ቀን ነው።

59. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 68 ከዚህ በታች ከተመለከቱት መደቦች በአንደኛው ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ግብር ከፋይ የገንዘብ

ሚኒስትራችን እንዲሠራባቸው በደንብ የሚያወጣቸውን ሂሳቦች መዝገቦች የማይዝ ግብር ከፋይ በሚከፍለው ግብር ላይ በመቶ ሃያ (20) መቀጫ ይከፍላል።

60. አዋጅ ቁ. 173/1953 (እንደተሻሻለው) 11ኛ <u>የግብር አከፋፈል</u> ከአንቀጽ 44-46 ጥምር።

61. አዋጅ ቁ. 173/1953 (እንደተሻሻለው) 10ኛ <u>የግብር አወሳሰን</u> ከአንቀጽ 38-43. ጥምር

62. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ. 2974። የማይገባውን ስለ መክፈል።</u>

1. ሊከፈል የማይገባውን ነገር የከፈለ ሰው እንዲመለስለት የመጠየቅ መብት አለው።
2. የሚከፈለው ነገር የተቀበለው እምነትን የሚያጎድል ሁኔታ እንደሆነ የማይገባውን ነገር የከፈለው ሰው ከከፈለበት ቀን አንስቶ ይህ የከፈለው ነገር የሰጠውን ፍሬ ወይም ሕጋዊውን ወለድ ጥምር እንዲመለስለት ለመጠየቅ ይችላል።

63. አዋጅ ቁ 77/1967 (እንደተሻሻለው), አንቀጽ 26.

64. አዋጅ ቁ 205/1955 (እንደተሻሻለው), አንቀጽ 15 (ሐ)፣ ባለፋብሪካስ የየወሩን መግለጫ (ዲክላሬሽዮን) አቅርቦና ቀረጡንም በተወሰነው ጊዜ ከከፈለ በኋላ መግለጫ (ዲክላሬሲዮን) ለቀረው ባለሥልጣን ከቀረበበት ቀን አንስቶ እስከ አምስት (5) ዓመት ድረስ የተለየ የሂሳብ መጠየቂያ ውሳኔ ካልቀረበለት

በመጓጓዣው (በዲክላሬሲዮን) 15 (ሐ) የተደነገገው በመግለጫው (በዲክላሬሲዮኑ) ላይ ላልተመለከተው ገቢ ቀረጥ ከመክፈል ነፃ አያደርገውም።

65. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 66 ከዚህ በታች በ35ኛው አንቀጽ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ የሥራውን ገቢ ያላስታወቀ ማናቸውም ግብር ከፋይ በመጨረሻ ያገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን በሚወሰነው ግብር ላይ በተጨማሪ በመቶ ሃያ (20) መቀጫ ይከፍላል።

66. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 67^E ግብሩ ከሚከፈልበት ቀን ጀምሮ እስከ ሠላሳ (30) ቀን ድረስ ግብሩን በሙሉ ላይከፍል የቀረ ማናቸውም ግብር ከፋይ፣ ለየሰላሳው (30) ቀን ከግብሩ በላይ በመቶ ሁለት (2) መቀጫ እየተጨመረበት ይከፍላል። ጠቅላላው የመቀጫው ድምር በመቶ ሃምሳ (50) አያልፍም።

67. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው አንቀጽ 37 የገቢው ማስታወቂያ የሚሰጠው፣ ግብር የሚከፈልበትን ገቢ ለመወሰን የሚያስችል የገቢና የወጪ ዝርዝር ያለበት ያገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን በሚሰጠው ልዩ ፎርም ነው።

68. <u>የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁ. ፲ 1852 የይርጋ ማቋረጥ ውጤት።</u>

1. ይርጋው ከተቋረጠበት ጀምሮ እንደገና አዲስ የይርጋ ዘመን መቆጠር ይጀምራል።

2. ዕዳው በአንድ ማስረጃ ወይም በአንድ ዋርድ የተረጋገጠ እንደሆነ አዲስ የይርጋ አቆጣጠር ዘመን ሁል ጊዜ ዐሥር ዓመት ነው።

69. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለው) አንቀጽ 40

አንቀጽ 40 ግብር ከፋዩ ምንም ዓይነት የሂሳብ መዝገብና ሰነድ ያልያዘ እንደሆነ ወይም በማናቸውም ምክንያት የሂሳብ መዝገቡንና ሰነዱን ያገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን ያልተቀበለው እንደሆነ፣ ወይም ግብር ከፋዩ ከዚህ በላይ በ35ኛው አንቀጽ በተወሰነው ጊዜ እንደሆነ፣ የአገር ውስጥ ገቢ መ/ቤት ባለሥልጣን የግብሩን ልክ በግምት ሊወስን ይችላል። (ሰርዝ የተጨመረ)

70. አዋጅ ቁጥር 173/1953 (እንደተሻሻለው)

አንቀጽ 55 ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው የግብሩ ውሳኔ ማስታወቂያ ለግብር ከፋዩ ከተሰጠበት ቀን አንስቶ በሰላሳ (30) ቀን ውስጥ ነው። ይግባኝ ባዩ በዚህ በተባለው ጊዜ ውስጥ ምንም ይግባኝ ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፣ ወይም በዚሁ ጊዜ ውስጥ በአንቀጽ 54 በንዑስ አንቀጾች (ለ)፣ (ሐ)፣ (መ) ወይም (ሠ) የተወሰነውን ገንዘብ ባያሲዝ ወይም ሳይከፍል የቀረ እንደሆነ በአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን የተወሰነው ግብር ትክክለኛና የመጨረሻ ውሳኔ ሆኖ በዚያው መሠረት በፍጥነት ይፈጸማል።

71. የአዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 62ን ይመለከቷል።

72. የአዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 57 ና 61ን ይመለከቷል።

73. የአዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) ከአንቀጽ 58-6 ይመለከቷል።

74. ከእንግሊዝኛው ቅጂ በመለየት የአማርኛው ቅጂ አንቀጽ 706 (1) "በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 41 እና በዋናው አዋጅ በአንቀጽ 55 የተመለከቱት ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው..." በማለት ይናገራል። ታዲያ የአማርኛውን ቅጅ ተከትሎ የሚፈፀም ከሆነ የአንቀጽ 7(ሐ)ን ዓላማ ሙሉ በሙሉ ተርጓሚ የሚያደርገው ሆኖ ይታያል።

75. አዋጅ ቁ 173/1953 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 70 (ሐ)

አንቀጽ 70 (ሐ) በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 41 እና በዋናው አዋጅ በአንቀጽ 55 የተመለከቱት ውሳኔዎች እንደተጠበቁ ሆነው ግብር ከፋዩ፥

1. የገቢውን ሙሉና ትክክለኛ መግለጫ ያላቀረበ ሆኖ ቢገኝ

2. ስለገቢው ምንጮች ወይም ልኮች ወይም ስለሥራው መጠን መግለጫ ለማቅረብ እምቢተኛ የሆነ እንደሆነ፥ ወይም የሐሰት መግለጫ ለግብሩ ባለሥልጣን ያቀረበ እንደሆነ ወይም

3. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት የሚያስቀጣ ማናቸውም ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ፣ የአገር ውስጥ ገቢ መሥሪያ ቤት ባለሥልጣን ስጥፋት አባልፎት የነበረውን ማናቸውንም የግብር ውሳኔና ምደባ በማንኛውም ጊዜ ሽሮ ሌላ የግብር ውሳኔና ምደባ ለማድረግ ሥልጣን ሰጥቶታል።

“ማናቸውም ጥፋት” የሚለው አባባል ግብር ነክ የሆኑ ጥፋቶችን ብቻ እንደሚመለከት ሆኖ መተርጎም ይኖርበታል።

76. የአንቀጽ 70 (ሐ) ድንጋጌን በአንቀጽ 41 በተገለጸው ሁኔታ ላይ ተፈፃሚ ማድረግ አስቸጋሪ ሆኖ ይታያል። ይህ የሆነበት ምክንያት በግብር አስገቢው ባለሥልጣን በተለመደ ትርጉሙ ተደም ቢል የተደረገ የግብር ውሳኔ ባለመኖሩ ነው። በመሆኑም በአንቀጽ 41 መሠረት እንደ ፀደቀ ተቆጥሮ በግብር ተከፋይ የሚሆንበትን በገቢ ማስታወቂያ ላይ የተገለፀውን ገቢ እንደ ባለሥልጣኑ የመጀመሪያ የግብር ውሳኔ አድርጎ ከመውሰድ በቀር ሌላ አማራጭ አይኖርም።

77. እዚህ ላይ በአንቀጽ 70(ሐ) የተሰጠው ተላልፎ የነበረን የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ የመከለስ መብት አንድ ጉዳይ ለግብር ይግባኝ ኮሚሽዮን ወይም ለመደበኛ የይግባኝ ፍ/ቤቶች ቀርቦ ውሳኔ ባገኘበት ሁኔታ ላይ ተፈፃሚነት እንደሌለው መጠቆም እንወዳለን።